

# ወላጆች በ ልዩ ትምህርት ውስጥ ያላቸውን መብት የሚመለከት መምሪያ

## የልዩ ትምህርት የአሰራር ዋስትናዎች ማስታወቂያ

ሚያዝያ 2017

Ohio Department of Education

## ልዩ ትምህርትን በተመለከተ

ዕድሜያቸው ከ3 እስከ 21 ዓመት ለሆኑ ተማሪዎች የሚሰጥ ልዩ ትምህርት በፌዴራልና በግዛት **መስፈርቶች የሚመራ ነው፡ ፡** የፌዴራል መስፈርቶችም የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ደንብ (IDEA) ተብለው ይጠቀሳሉ። የግዛት መስፈርቶች ደግሞ የኦሃዮ የአካል ጉዳተኛ ሕጻናት ትምህርት የአሰራር መስፈርቶች (የኦሃዮ የአሰራር መስፈርቶች) ተብለው ይጠራሉ።

ይህ መምሪያ በ IDEA እና በኦሃዮ የአሰራር መስፈርቶች መሰረት እርስዎንና የልጅዎን መብቶች እንዲገነዘቡ ሊያግዝዎት ይችላል። የልጅዎ የልዩ ትምህርት ድጋፎችና አገልግሎቶች እንዲገነዘቡ የሚያስችል መረጃና ግብአትም ይሰጥዎታል።

የአካባቢዎ ት/ቤት ዲስትሪክትም በዚህ ሕግ መሰረት ያሉዎትን መብቶች እንዲረዱ ሊያግዝዎት ይችላል። በዚህ መምሪያ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ ለዲስትሪክትዎ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ያሳውቁ።

## የልዩ ትምህርት የት/ቤትዎ የግንኙነት ተጠሪ

ዲስትሪክት፡ *እባክዎ በዚህ አሳታፊ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚከተለውን መረጃ ያካትቱ፡*

**የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር፡**

**ስልክ ቁጥር፡**

**የኢሜይል አድራሻ፡**

### Ohio Department of Education Contact for Special Education

(ስልክ ቁጥር) 614-466-2650

(ከክፍያ ነጻ) 877-644-6338

(ፋክስ) 614-728-1097

25 S. Front Street, Mail Stop 409
Columbus, Ohio 43215

Exceptionalchildren@education.ohio.gov

ቴሌታይፕራይተር ለሚጠቀሙ ደዋዮች (ቲቲዋይ)፣ እባክዎ ለኦሃዮ ሪሌይ ሰርቪስ በስልክ ቁጥር (800) 750-0750 ይደውሉ።

ተጨማሪ የመገኛ መረጃ http://bit.ly/2hgiNa1

## የዚህ የወላጆች መብቶች መምሪያ መግቢያ

የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ደንብ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች መብትና ለወላጆቻቸው መብቶች ጥበቃ ያደርጋል። ይህ መምሪያ እነዚያን መብቶች በተመለከተ መረጃ ይሰጡዎታል። ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያገኝ ከሆነ፣ ት/ቤትዎ የመምሪያውን ቅጂ በዓመት አንድ ጊዜ ሊሰጥዎት ይገባል። በሚከተሉት ሁኔታዎችም ቅጂ ማግኘት አለብዎ፡

- ልጅዎ አካል ጉዳት ሊኖርበት ይችላል ብለው በማሰብዎ ምክንያት ልጅዎ ምዘና እንዲካሄድለት ከጠየቁ፤
- የት/ቤት ዲስትሪክትዎ ልጅዎ አካል ጉዳት ሊኖርበት ይችላል ብለው በማሰብዎ ምክንያት ልጅዎ ምዘና እንዲካሄድለት ከጠየቀ፤
- በOhio Department of Education ስር ለሚገኘው Office for Exceptional Children *ቅሬታ* በጽሑፍ ካቀረቡና ይህም ቅሬታዎ በትምህርት ዘመኑ *የመጀመሪያ* ቅሬታዎ ከሆነ፤
- በOhio Department of Education ስር ለሚገኘው Office for Exceptional Children የልጅዎን ትምህርት በተመለከተ *የመደበኛ ሒደት ችሎት* እንዲዘጋጅልዎ የጽሑፍ ጥያቄ ካቀረቡና ይህም ጥያቄዎ በትምህርት ዘመኑ የመጀመሪያ ጥያቄዎ ከሆነ፤
- ልጅዎ *በዲስፕሊን (የባህርይ) ምክንያት ከት/ቤት ከተባረረና* ልጅዎም በዚህ የትምህርት ዘመን ለ10 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት የተባረረ ከሆነ፤ ወይም
- *የመምሪያው ቅጂ እንዲሰጥዎ በሚጠይቁበት በማንኛውም ወቅት፡*



## ማውጫ

**አጠቃላይ መረጃ ............ 5**

በመረጃ የታገዘ የወላጆች ፈቃድ
ልጅዎ ለልዩ ትምህርት ብቁ ነው?
ራሳቸውን የቻሉ ትምህርታዊ ምዘናዎች
በቅድሚያ የሚሰጥ የጽሑፍ ማስታወቂያ

**ትምህርታዊ መረጃዎች............ 10**

የመረጃዎች ተደራሽነት

**የግጭት አፈታት ............ 12**

የግጭት አፈታት ሒደት
የቅድሚያ ቅሬታ አፈታት
ማቀላጠፍ
ማስታረቅ
የግዛት ቅሬታ ማቅረብ
የግዛት ቅሬታ ሒደት
ለመደበኛ የዳኝነት ስርዓት አቤቱታ ማቅረብ
የመደበኛ የዳኝነት ስርዓት የጊዜ ገደብና ሒደት
በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት መፍትሔ መስጠት
የችሎት ሒደት
ውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ
በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ወቅት የልጁ ሁኔታ
የጠበቃ ወጪ

**ስነ ስርዓት ............ 29**

አካል ጉዳተኛ ሕጻናት ላይ የሚተገበሩ የዲስፕሊን አሰራሮች
የማኒፌስቴሽን አወሳሰን
ጊዜያዊ የአማራጭ (ጊዜያዊ እና የተለየ) ትምህርት ማዕቀፍ

**የአካል ጉዳተኛ ልጆች ስነ ስርዓት አሰራሮች በተግባር ማሳየትን መወሰን ጊዜያዊ የአማራጭ ትምህርት ማዕቀፍ ወላጆች አካል ጉዳተኛ ልጆችን በግል ት/ቤት በማስገባት ወጪው በመንግስት የሚሸፈንበት ሁኔታ ............ 32**

የወጪ ምልሰት አወሳሰን ሒደት

**የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ስኮላርሺፕ ፕሮግራሞችን ለወላጅ ማሳወቂያ............ 33**

ማሳወቂያ ሲላክ

# አጠቃላይ መረጃ

## በመረጃ የታገዘ የወላጅ ፈቃድ

በመረጃ የታገዘ የወላጅ ፈቃድ ማለት እርስዎ እና/ወይም በዲስትሪክት የተሾመ ተተኪ ወላጅ የት/ቤት ዲስትሪክቱ እርምጃ እንዲወስድ የጽሑፍ ፈቃድ ትሰጣላችሁማለት ነው። እርስዎ ፈቃድ ሰጡ ማለት ደግሞ ዲስትሪክቱ ሊወሰድ ስለታሰበው እርምጃ መረጃ ሰጥቶዎታል ማለት ነው። የልጅዎ ት/ቤት ዲስትሪክት ከልጅዎ ልዩ ትምህርት ጋር የተያያዙ የተወሰኑ ነገሮችን ለመፈጸም ከእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት። የት/ቤት ዲስትሪክቱ የእርስዎን የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያለበት፡

- ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት መሆኑን ለማወቅ ዲስትሪክቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ልጅዎ ላይ ምዘና ከማካሄዱ በፊት፤
- ዲስትሪክቱ በመጀመሪያው ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም ወይም IEP ውስጥ የተዘረዘሩ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ለልጅዎ መስጠት ከመጀመሩ በፊት፤
- ዲስትሪክቱ የልጅዎ ፍላጎቶች መቀየራቸውን ለማወቅ በልጅዎ ላይ ዳግም ምዘና ከማካሄዱ በፊት፤
- ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ ተጨማሪ ምዘናዎችን ከማካሄዱ በፊት። ተግባራዊ የባህርይ ምዘና ምሳሌ ሊሆን ይችላል፤
- ዲስትሪክቱ የልጅዎን የትምህርት ምደባ ከመቀየሩ በፊት። ይህ ግን የግድ የአድራሻ ለውጥ ማለት አይደለም። ከዚህ ይልቅ፣ በልጅዎ የትምህርት ፕሮግራም ላይ የተደረገ ለውጥ ማለት ነው፤ እና
- ዲስትሪክቱ በግዛት ወይም በፌዴራል ሕግ ውስጥ ከተዘረዘሩት ውጭ ላሉ ሰዎች ልጅዎን በተመለከተ መረጃ ከመስጠቱ በፊት።

### ተተኪ ወላጅ ምንድን ነው?

ተተኪ ወላጅ ማለት አካል ጉዳተኛ የሆነ ልጅን ወክሎ ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ከመሆን ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚያከናውን ግለሰብ ነው።

የሚከተሉት ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ወቅት እርስዎ የሚኖሩበት ት/ቤት ዲስትሪክት ተተኪ ወላጅ ይሾማል፡

- የወላጅ ማንነት ሊታወቅ ካልቻለ፤
- የት/ቤት ዲስትሪክቱ ተገቢውን ጥረት ካደረገ በኋላ የወላጅን አድራሻ ማወቅ ካልቻለ፤
- ልጁ ብቸኛና ቤት አልባ ወጣት ከሆነ፤ ወይም
- ልጁ በግዛት አደራ ስር ከሆነ ነው።

**ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ የትኛውም ቢከሰት በመረጃ የታገዘ የወላጅ ፈቃድ አያስፈልግም፡**

- ዲስትሪክቱ በሚያካሂደው የምዘና/ዳግም ምዘና ሒደት ምክንያት ነባር የተማሪ መረጃን እየከለሰ ሲሆን፤ ወይም
- ዲስትሪክቱ በሁሉም ተማሪዎች ላይ የሚካሄዱ ምዘናዎችን በልጅዎ ላይ ሲያካሂድ ነው።



## በመረጃ የታገዘ የወላጅ ፈቃድ ለመስጠት፣ ዲስትሪክቱ፡

- ውሳኔ ለመወሰን የሚያስችልዎትን መረጃ በሙሉ እንዲያገኙ ለማስቻል የእርስዎን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም ሌላ ሊረዱት የሚችሉ የግንኙነት ዘዴን መጠቀሙን ማረጋገጥ አለበት፤
- ዲስትሪክቱ አንድን ተግባር እንዲያከናውን መስማማትዎን በጽሑፍ እንደገለጹና የሰጡትም ፈቃድ ተግባሩን እንደዚሁም ከሌሎች እና ከማን ጋር የሚጋሩ ማናቸውንም የልጅዎን መረጃዎች የሚገልጽ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤
- ፈቃድዎን የሚሰጡት በራስዎ ምርጫ መሆኑንና በማንኛውም ወቅት ሃሳብዎን ለመቀየር እንደሚችሉ የተገነዘቡ መሆንዎትን ማረጋገጥ አለበት፤
- ፈቃድዎን ከሻሩ፣ ዲስትሪክቱ እርስዎ ፈቃድ በሰጡበትና ፈቃዱን በሻሩበት ጊዜ መካከል ባለው ጊዜ የወሰደውን ማንኛውም እርምጃ እንደማይቀለብስ መገንዘብዎን ማረጋገጥ አለበት።

## ፈቃድን መሻር

ፈቃድን መሻር ማለት የሰጡትን ፈቃድዎን ያነሳሉ ማለት ነው። ልጅዎ በልጅዎ IEP ውስጥ የተገለጹትን የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እንዳያገኝ ከወሰኑ፣ ቀደም ሲል የሰጡትን ፈቃድ በማንኛውም ጊዜ መሻር ይችላሉ። ይህን ማድረግ ያለብዎት ***በጽሑፍ*** ነው።

ከዚያም፣ የት/ቤት ዲስትሪክትዎ፡

- በ ውስጥ ያሉትን የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ለልጅዎ መስጠቱን ማቋረጥ አለበት፣ አገልግሎት መስጠቱን ከማቆሙ በፊት ግን ዲስትሪክቱ አገልግሎት ሊያቋርጥ እንደሆነ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ሊሰጥዎት ይገባል። በዲስትሪክቱ የሚሰጥዎት ማስታወቂያ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይባላል። ይህ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ በዚህ መምሪያ ገጽ 9 ላይ በቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ክፍል ውስጥ ያሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

ዲስትሪክቱ ለልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መስጠቱን እንደሚያቆም የሚገልጽ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ከሰጠዎትና አገልግሎቱም አንዴ ካቆመ፣ ዲስትሪክቱ ልጅዎን ለልዩ ትምህርት ብቁ አድርጎ የማይቆጥረው ሲሆን ልጅዎም እንደ መደበኛ ትምህርት ተማሪ ይቆጠራል።



## ልጅዎ ልዩ ትምህርት ለማግኘት ብቁ ነው?

ብቁ መሆን ማለት፣ ልጅዎ ባለበት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የአካል ጉዳት ምክንያት የተወሰኑ የትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል ማለት ነው። የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ደንብ (IDEA) አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልዩ ትምህርት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይደነግጋል። በዚህ ሕግ መሰረት አካል ጉዳተኛ ተማሪ ተብሎ ለመቆጠር፣ ልጅዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የአካል ጉዳት ምድቦች ምክንያት ባለበት አካል ጉዳት የተነሳ ልዩ ትምህርት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚስፈልጉት መሆን አለበት፦

- አእምሯዊ አካል ጉዳት፤
- የመስማት ችሎታ መሳን፤
- የንግግር ወይም የቋንቋ መሳን
- ማየት መሳን፤
- የስሜት መታወክ፤
- የአጥንት ጤና መታወክ፤
- ኦቲዝም፤
- ጉዳት አዘል የአንጎል ጉዳት፤
- ሌላ የጤና ችግር፤
- ውስን የመማር ችሎታ መሳን፤
- መስማት አለመቻል፤
- ማየትም ሆነ መስማት አለመቻል፤
- ከአንድ በላይ የአካል ጉዳት፤ ወይም
- የዕድገት መዘግየት።

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም ሌላ የግንኙነት ዘዴ**

**እርስዎ የሚሳተፉባቸው ስብሰባዎች በሙሉ፣ የልጅዎ ምዘና እና የሚደርሱዎት ሁሉም ማስታወቂያዎች በእርስዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም እርስዎ በሚጠቀሙት ሌላ የመግባቢያ ዘዴ መጻፍ ወይም መነገር አለባቸው።**

**ልጅዎን ለመመዘን የሚያገለግሉ ምርመራዎችና ሌሎች ማቴሪያሎች በልጅዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በሌላ የመግባቢያ ዘዴ መካሄድ ያለባቸው ሲሆን ይህም ለማቀውረብ ወይም ለማስተዳደር አስቸጋሪ ካልሆነ በስተቀር ልጅዎ በአካዳሚክ፣ በእድገትና በተግባር ረገድ ስለሚያውቀው ነገር ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ የሚሰጥ መሆን አለበት።**

### ዲስትሪክቱ ልጅዎ ላይ ምዘና እንዲያካሄድ ይጠይቁ

ልጅዎ በትምህርቱ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር የአካል ጉዳት አለበት ብለው ካሰቡ፣ ለልዩ ትምህርት ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን (በIDEA መሰረት አካል ጉዳተኛ ሕጻን ተደርጎ እንዲቆጠር) ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ ምዘና እንዲያካሂድ መጠየቅ ይችላሉ። የዲስትሪክት ሠራተኞች ልጅዎ ልዩ ትምህርት ሊያስፈልገው ይችላል ብለው ካሰቡም ልጅዎ ላይ ምዘና እንዲካሄድ የሚፈልጉ መሆንዎትን የት/ቤቱ ዲስትሪክት በማንኛውም ጊዜ ሊጠይቅዎት ይችላል። በሁለቱም ሁኔታ ቢሆን፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ የእርስዎን የጽሑፍ ፈቃድ ካገኘ በኋላ የመጀመሪያውን ምዘና በ60 የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት።

### ልጁ በግዛት አደራ ስር ከሆነ

ልጁ በግዛት ***አደራ ስር ከሆነና*** ከወላጆቹ ጋር የማይኖር ከሆነ፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ ልጅዎ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት አካል ጉዳተኛ ልጅ መሆኑን ለመወሰን የመጀመሪያ ምዘና ለማካሄድ የወላጅን ፈቃድ ማግኘት አያስፈልገውም፦

- የት/ቤት ዲስትሪክቱ ተገቢ ጥረቶችን ቢያደርግም የልጅዎን ወላጅ አድራሻ ለማግኘት ካልቻለ፤
- የወላጆች መብቶች ተቋርጠዋል፤ ወይም
- የወላጆች መብቶች ለመጀመሪያው ምዘና ፈቃዱን ለሰጠ ወላጅ በዳኛ ውሳኔ ከተላለፉ።

## ገለልተኛ የትምህርት ምዘናዎች (IEE)

ገለልተኛ የትምህርት ምዘና ውጫዊ ምዘና (IEE) እየተባለም ይጠራል። የት/ቤት ዲስትሪክቱ የዚህን ውጫዊ ምዘና ወጪ የሚሸፍነው በልጅዎ ላይ የራሱን ምዘና ቀደም ሲል ካካሄደና እርስዎም በዲስትሪክቱ ግኝት ካልተስማሙ ብቻ ነው። የምዘናው ዓላማም ልጅዎ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልገው መሆኑን ወይም ልዩ ትምህርት የሚያስፈልገው መሆኑ እንደሚቀጥል ለማወቅ ነው። በዚህ ውጫዊ ምዘና ላይ ለልጅዎ ምዘናውን የሚያካሂደው ሰው የልጅዎ ት/ቤት ዲስትሪክት ሠራተኛ መሆን አይችልም። እርስዎም ወላጅ በመሆንዎ በማንኛውም ጊዜ ለልጅዎ ውጫዊ ምዘና ማመቻቸትና ወጪውን የመሸፈን መብት አለዎት። ዲስትሪክትዎ በልጅዎ ላይ ባደረገው ምዘና ካልተስማሙና ውጫዊ ምዘና እንዲካሄድ ከጠየቁ፣ ዲስትሪክትዎ ከእነዚህ እርምጃዎች መካከል አንደኛውን በፋጣኝ መውሰድ አለበት፡

- የት/ቤት ዲስትሪክቱ በራስዎ ወጪ ለልጅዎ ውጫዊ ምዘና የት ማግኘት እንደሚችሉ ሊነግርዎት የሚገባ ሲሆን ዲስትሪክቱ ወጪውን እንዲሸፍን መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶችም ሊያሳውቅዎት ይገባል። ከዲስትሪክቱ ባገኙት ስምምነት መሰረት ውጫዊ ምዘና ከተካሄደ፣ ዲስትሪክቱ ወጪውን መሸፈን አለበት፤ ወይም
- ዲስትሪክቱ እርስዎ ያቀረቡትን የውጫዊ ምዘና ጥያቄ ባለመቀበሉ የመደበኛ ዳኝነት ችሎት (ገጽ 21ን ተመልከት) እንዲመቻች ለOhio Department of Education's Office for Exceptional Children ጥያቄ ማቅረብ አለበት። የዚህ ምክንያት ደግሞ ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ ያካሄደው ምዘና አግባብነት አለው ብሎ ስለሚያስብ ነው።


### የውጫዊ ምዘናዎች መስፈርት

ዲስትሪክቱ በሚያካሂዳቸው ምዘናዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ተመሳሳይ መስፈርቶች ወላጆች በሚያመቻቹትና ዲስትሪክቱ ወጪያቸውን በሚሸፍንላቸው ውጫዊ ምዘናዎች ላይም ተፈጻሚነት አላቸው። ከእነዚህ መስፈርቶች መካከልም ልጅዎ ምዘናውን የሚያካሂድበት ቦታና ልጅዎን የሚመረምረው ግለሰብ የስራ ልምድ ይገኙበታል። ዲስትሪክቱ የራሱን መስፈርቶች የሚያሟላ ውጫዊ ምዘናን ሙሉ ወጪ መሸፈን አለበት።

በልጅዎ ላይ ውጫዊ ምዘና እንዲካሄድ ከጠየቁ፣ ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ ባካሄደው ምዘና ***ለምን*** እንዳልተስማሙ  (ይህም ማለት፣ ውጫዊ ምዘና የፈለጉባቸውን ምክንያቶች) ዲስትሪክቱ ሊጠይቅዎት ይችላል፤ ነገር ግን፣ እርስዎ ካልፈለጉ በስተቀር ይህን ማስረዳት አይገደዱም። ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ ምዘና ባካሄደና በዲስትሪክቱ የምዘና ውጤቶችም ባልተደሰቱ ቁጥር እርስዎም አንድ ውጫዊ ምዘና ወጪው ተሸፍኖ እንዲካሄድልዎ የመጠየቅ መብት አለዎት።

ልጅዎ የዲስትሪክቱን መስፈርቶች የሚያሟላ ውጫዊ ምዘና አንዴ ከተደረገለት፣ የምዘናው ወጪ የሚሸፈነው በማንም ቢሆን ዲስትሪክቱ የምዘናውን ውጤቶች ታሳቢ በማድረግ ለልጅዎ ከክፍያ ነጻ የሆነ አግባብነት ያለው የመንግስት ትምህርት እንዴት እንደሚሰጥ መወሰን አለበት (FAPE)።

**የሚከተለው ቻርት እርስዎ ውጫዊ ምዘና ሲጠይቁ የሚከሰቱ የተለያዩ ምናባዊ ታሪኮችን ያሳያል**



# የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ

## አጠቃላይ መግለጫ

የት/ቤት ዲስትሪክቱ የተወሰኑ እርምጃዎችን ከመጠቆሙ ወይም ላለመውሰድ ከመወሰኑ በፊት ምክንታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ የጽሑፍ ማስታወቂያ (የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ተብሎ ይጠራል) ሊሰጥዎት ይገባል። ከእነዚህ እርምጃዎችም መካከል ዲስትሪክቱ የልጅዎን ልየታ፣ ምዘና ወይም ትምህርታዊ ምደባ ወይም ለልጅዎ አግባብነት ያለው ነጻ የመንግስት ትምህርት መስጠትን ማስጀመር ወይም መለወጥ ይገኝበታል። የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ አስፈላጊ የሆነ የልዩ ትምህርት ቅጽ ነው።

## የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይዘቶች

የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ እርስዎ በመረጃ በታገዘ መልኩ በልጅዎ ትምህርታዊ አገልግሎቶች ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያስችልዎትን በቂ ዝርዝር ማቅረብ አለበት። በተለይም፣ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ በዚህ ገጽ አባሪ ሳጥን ውስጥ የተዘረዘሩትን የተወሰኑ ይዘቶች ማካተት አለበት።

## የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ አንባቢው በሚረዳው ቋንቋ መዘጋጀት አለበት

የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ አጠቃላዩ ሕዝብ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ይህን ማድረጉ የማይቻል ካልሆነ በስተቀር በእርስዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም ሌላ የመግባቢያ ዘዴ መጻፍ አለበት።

የወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም ሌላ የግንኙነት ዘዴ የሚጻፍ ቋንቋ ***ካልሆነ*** ፣ ዲስትሪክቱ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ በወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ በቃል ለማስተርጎም ወይም ወይም በሌላ የግንኙነት ዘዴ ለማቅረብ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። ዲስትሪክቱ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያው አግባብነት ባለው መንገድ መተርጎሙንና ወላጆችም ይዘቱን መረዳታቸውን በጽሑፍ ማሳየት እንደሚችል ማረጋገጥ አለበት።

### የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ማካተት ያለበት፡

- ዲስትሪክቱ የጠቆመው ወይም ያልተቀበለው እርምጃ መግለጫ፤
- ዲስትሪክቱ እርምጃውን ለምን እንደጠቆመ ወይም እንዳልተቀበለ ማብራሪያ፤
- ት/ቤቱ ውሳኔውን ለማሳለፍ የተጠቀማቸው የእያንዳንዱ የምዘና አሰራር ሒደት፣ ምዘና፣ መዝገብ ወይም ሪፖርት መግለጫ፤
- ወላጆች በIDEA የአሰራር ዋስትና ጥበቃ እንዳላቸው የሚያትት መግለጫ፣ እንደዚሁም ማስታወቂያው ለምዘና የመጀመሪያ ሪፈራል ካልሆነ፣ አንድ ወላጅ የአሰራር ዋስትናዎችን መግለጫ የሚያገኝበትን መንገድ መግለጫ።
- ወላጆች የIDEA መስፈርቶችን በመረዳት ረገድ እገዛ ሲፈልጉ የሚያናግሩትን ሰው አድራሻ፤
- የIEP ቡድን ከግምት ውስጥ ያስገባቸውን ሌሎች አማራጮችና እነዚያ አማራጮች ውድቅ የተደረጉባቸውን ምክንያቶች፤
- ከዲስትሪክቱ ጥቆማ ወይም አለመቀበል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ጉዳዮች መግለጫ።



# ትምህርታዊ መረጃዎች

## የመረጃዎች ተደራሽነት

የቤተሰብ የትምህርት መብቶችና ግላዊነት ደንብ (FERPA) ወላጆች የልጆቻቸውን የትምህርት ማስረጃዎች የመመርመርና የማየት መብት የሚሰጥ የፌዴራል ሕግ ነው፡ ፡ ተማሪው ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላው ወይም ድሕረ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት (ለምሳሌ፡ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ) ሲገባ በFERPA ስር ያሉት መብቶች ከወላጆች ወደ ተማሪው ይተላለፋሉ።

### የትምህርት ማስረጃዎች ምንድን ናቸው ?

አንድን ተማሪ የሚመለከት የተወሰነ መረጃ በFERPA ከለላ የሚሰጠው ጉዳዩ የትምህርት ማስረጃ ትርጉምን በማሟላቱ ላይ ተመስርቶ ነው። FERPA ለትምህርት ማስረጃ የሚሰጠው ፍቺ፡

1. ከአንድ ተማሪ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ማስረጃዎች። አንዳንድ ጊዜ ት/ቤቶች የግለሰብን ማንነት የሚገልጽ መረጃ ብለው ይጠሩታል፤
2. አንድ የትምህርት ኤጀንሲ ወይም ተቋም (ለምሳሌ የእርስዎ የት/ቤት ዲስትሪክት) ወይም ኤጀንሲ ወክሎ የሚሰራ አካል የሚይዛቸው ማስረጃዎች።

### ማስረጃዎችን ይዞ ማቆየትና ሚስጥራዊነት

የትምህርት ማስረጃዎች በበርካታ መንገዶች ይዞ ማቆየት ይቻላል። አንዳንድ ምሳሌዎች፡

- በእጅ የተጻፈ፤
- የታተመ፤
- ኮምፒዩተር፤
- የቪድዮ ወይም የድምጽ ቅጂ፤ ወይም
- ፊልም፣ ማይክሮ ፊልም ወይም ማይክሮፊሽ።

የተማሪ ማስረጃዎች ሚስጥራዊ ናቸው፣ ማለትም ***ግላዊ*** ናቸው። የት/ቤት ዲስትሪክት ወይም ኤጄንሲ የልጅዎን ማስረጃዎች ሲሰበስብ፣ ሲያከማች፣ ሲያስተላልፍ ወይም ሲያስወግድ ግላዊነቱን መጠበቅ አለበት።

### የልጅዎን ማስረጃዎች ማየት

የት/ቤት ዲስትሪክቱ አላስፈላጊ መዘግየት ሳይፈጥርና የማንኛውም IEP ቡድን ስብሰባ ወይም እርስዎ ተሳታፊ የሆኑበት መደበኛ የዳኝነት ሒደት ከመጀመሩ በፊት የልጅዎን የትምህርት ማስረጃዎች እንዲያዩ ሊፈቅድልዎት ይገባል። ዲስትሪክቱ እርስዎ ማስረጃዎቹን ለማየት ከጠየቁበት ቀን አንስቶ ከ45 ቀናት በላይ መውሰድ የለበትም።

ከማስረጃው ውስጥ ማየት የሚችሉት ***ልጅዎን*** የሚመለከቱ መረጃዎችን ብቻ ነው። ት/ቤቱ የልጅዎን ማስረጃዎች እንዲያብራራ የመጠየቅ መብት አለዎት። የእርስዎ ወኪል የሆነ ሰው (ጓደኛ ወይም ጠበቃ) ማስረጃዎቹን እንዲያይ የመሾም መብት አለዎት።

ዲስትሪክቱ የልጅዎን ማስረጃዎች ኮፒ ሊሰጥዎት ይችላል፤ ይሁን እንጂ ዲስትሪክቱ ኮፒውን የመስጠት ግዴታ ***ያለበት*** ኮፒውን እርስዎ ማስረጃዎችን የማየት መብትዎን ከመተግበር የሚያግድዎት ሲሆን ነው። በራስዎ ወጪ የማስረጃዎችን ኮፒ የማግኘት መብት አለዎት።

**ማንነትን የሚገልጽ መረጃ ውስጥ የሚካተቱ፡**

- **የልጅዎ ስም፤**
- **የቤተሰብ አባል ስም፤**
- **የልጅዎ አድራሻ ወይም የቤተሰብ አድራሻ፤**
- **ማንነትን የሚገልጽ መረጃ፣ ለምሳሌ የልጅዎ ማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር፣ የተማሪ ቁጥር ወይም የባዮሜትሪክ መረጃ፤**
- **ልጅዎን ለመለየት የሚውሉ ሌሎች ተዘዋዋሪ መረጃዎች፣ ለምሳሌ የትውልድ ዘመን፣ የትውልድ ቦታ፣ የእናት የአባት ስም፣ ዘር ወይም ብሔር፤**
- **ብቻውን ወይም በጋራ ከአንድ ተማሪ ጋር የተሳሰረ ወይም ሊተሳሰር የሚችል መረጃ፣ አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች በተመለከተ ግላዊ እውቀት የሌለው በት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ያለ ሰው ተማሪውን በተወሰነ እርግጠኝነት ለመለየት የሚያስችለው መረጃ፤**
- **በት/ቤቱ እምነት የልጅዎን ማንነት በተመለከተ ግንዛቤ ያለው ሰው የሚጠይቀው መረጃ፤ ወይም**
- **ሌሎች ምሳሌዎች በFERPA ላይ ተቀምጠዋል።**



## የትምህርት ማስረጃዎች ላይ የሚደረጉ ለውጦች

በልጅዎ የትምህርት ማስረጃዎች ውስጥ ያለ የተሳሳተ ወይም አሳሳች መረጃነን የት/ቤት ዲስትሪክቱ እንዲቀይር የመጠየቅ መብት አለዎት። የልጅዎ ት/ቤት በእርስዎ ጥያቄ መሰረት (እርስዎ ስለጠየቁ ብቻ) የትምህርት ማስረጃዎችን መጠየቅ የለበትም፤ ነገርግን ት/ቤቱ ጥያቄዎትን ***ከግምት ውስጥ*** ማስገባት አለበት። ት/ቤቱ በእርስዎ ጥያቄ መሰረት የልጅዎን ማስረጃ ላለመቀየር ከወሰነ፣ ስለ ጉዳዩ ለመነጋገር ችሎት እንዲዘጋጅልዎ የመጠየቅ መብት እንዳለዎ ት/ቤቱ ሊነግርዎት ይገባል።

ከችሎቱ በኋላም ት/ቤቱ የልጅዎን ማስረጃ ላለመቀየር በውሳኔው ከጸና፣ በጉዳዩ ላይ ያለዎትን ሐተታ በልጅዎ ማስረጃ ውስጥ የማካተት መብት አለዎት። ሐተታውም የልጅዎ ማስረጃ አካል ሆኖ ይቆያል። በልጅዎ ማስረጃ ውስጥ ሐተታ የመጻፍ አማራጭ የሚኖረው ***ማስረጃዎቹ የተሳሳተ መረጃ ከያዙ ብቻ ነው***። ይህን ሐተታ ተጠቅመው ለልጅዎ የተሰጠውን ውጤት፣ ግለሰባዊ አስተያየት ወይም ት/ቤቱ ልጅዎን በተመለከተ ያሳለፈውን ውሳኔ መገዳደር አይችሉም።

## የትምህርት ማስረጃዎችን ማጋራት

አብዛኛውን ጊዜ፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ የልጅዎን የትምህርት ማስረጃ ከእርስዎ ውጭ ላለ ሰው ለማጋራት ሲፈልግ የእርስዎን የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት። ይሁን እንጂ፣ የእርስዎ ፈቃድ የማያስፈልግባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። የት/ቤት ዲስትሪክቱ ማስረጃዎችን ለማጋራት የእርስዎን ፈቃድ ***የማይፈልግባቸውን*** ጊዜያት ለማወቅ የ**FERPA የወላጆች አጠቃላይ መምሪያን** በU.S. Department of Education ድረ ገጽ ማየት ይችላሉ **www.ed.gov**፡



# የግጭት አፈታት

## የግጭት አፈታት ሒደት

የአካል ጉዳተኛ ልጅዎን ትምህርት በተመለከተ አሳሳቢ ሁኔታ ካለዎት፣ የመጀመሪያ እርምጃ የሚሆነው ከት/ቤትዎ ዲስትሪክት ጋር አብሮ መስራት ነው። ለመጀመር፣ ከልጅዎ መምህር ወይም ከዲስትሪክትዎ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ጋር ይነጋገሩ። ምን እንደሚያስቡም ይንገሯቸው። አሳሳቢ ሁኔታዎን በተመለከተ እርስዎና ዲስትሪክቱ ካልተስማማችሁ፣ ችግሩን ለመፍታት አብራችሁ የምትሰሩባቸው መንገዶች አሉ።

እነዚህ ሒደቶች የት/ቤት ዲስትሪክትዎ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ መደበኛ ስሞች አሏቸው፤ ነገር ግን እነዚያ ስሞች ምን ማለት እንደሆኑና እርስዎና ት/ቤቱ እንዴት ልጅዎን መርዳት እንደምትችሉ እንደትገነዘቡ ያግዛችኋል። ቀጣዩ ክፍል ከዲስትሪክትዎ ጋር ለመስራት የምትጠቀሙባቸውን ሒደቶች ወይም ዘዴዎች ይገልጻል።

### አስተዳደራዊ ክለሳ

የአካል ጉዳተኛ ልጅዎን ትምህርት በተመለከተ በት/ቤት ዲስትሪክትዎ ውሳኔ ካልተስማሙ፣ ለዲስትሪክትዎ አስተዳደር ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። በምላሹም የዲስትሪክት ዋና ተቆጣጣሪ (ወይም ተወካዩ) አስተዳደራዊ ክለሳ ያካሂዳል። ይህ ክለሳም አስተዳደራዊ ችሎትን ሊያካትት ይችላል።

ክለሳውና አስተዳደራዊ ችሎቱ መካሄድ ያለበት ለሁሉም ተሳታፊ አካላት ምቹ በሆነ ጊዜና በታ ነው። እርስዎና ዲስትሪክቱ ሌሎች ሰዎችን በክለሳው ወይም በአስተዳደራዊ ችሎት ላይ እንዲካፈሉ መጋበዝ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኛ፣ ስለ ልዩ ትምህርት እውቀት ያለው ሰው፣ ወይም ጠበቃ መጋበዝ ይችላሉ። ልጅዎ የሚማረው በካውንቲው የዕድገት አካል ጉዳት ቦርድ ወይም በሌላ መንግስታዊ የትምህርት ኤጄንሲ በሚመራ ፕሮግራም ከሆነ፣ ዲስትሪክቱ አስተዳደራዊ ችሎት እንዲዘጋጅ ከቦርዱ ወይም ከኤጄንሲው ጋር መመካከር አለበት።

ሁኔታው በሚገመገምበት ወቅት፣ የልጅዎን ትምህርት በተመለከተ አለመግባባቱን ለመፍታት ማንኛውም ጥረት መደረግ አለበት። ዋና ተቆጣጣሪ (ወይም ተወካዩ) የአለመግባባቱን ሁለቱም ወገኖች ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል። ውሳኔው አንዴ ከተላለፈ፣ ዋናው ተቆጣጣሪ ውሳኔውን በጽሑፍ ሊያሳውቅዎት ይገባል። ይህም መደረግ ያለበት እርስዎ አሳሳቢውን ጉዳይ ለ ዲስትሪክቱ ባሳወቁ በ20 ቀናት ውስጥ ነው።

### መሞከር የሚችሏቸው ሌሎች ሒደቶች

ይህን ሒደት ካጠናቀቁና እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ ችግሩ እንዴት እንደሚፈታ አሁንም ካልተስማማችሁ፣ መሞከር የሚችሏቸው ተጨማሪ ሒደቶች አሉ፡ ፡ ወደሌሎች የግጭት መፍቻ ሒደቶች ከመሻገርዎ በፊት አስተዳደራዊ ክለሳ መጠየቅ ባይገደዱም ይህን ማድረጉ ይበረታታል። ችግሩን ለመፍታት ሌሎች ተጨማሪ አማራጮችን መጠቀም ይችላሉ። የOhio Department of Education’s Office for Exceptional Children በጉዳዩ ገብቶ አሳሳቢ ጉዳዮችዎን ለመፍታት ያቀረቡትን ተጨማሪ አማራጭ በተመለከተ ሊያግዝዎት ይችላል። የሚከተሉት ድርጅቶችም ሊያግዙዎት ይችላሉ፡

- የአካባቢ ግዛት ድጋፍ ሰጪ ቡድን (የክልል ቁጥር #____________) (ስልክ ቁጥር ________________________)። በግዛት ድጋፍ ሰጪ ቡድን የሚገኘው የወላጅና የቤተሰብ አማካሪ ከእርስዎ ጋር አብሮ ይሰራል።
- የት/ቤት ዲስትሪክትዎ ካለው፣ የአካባቢ የወላጅ አማካሪዎ።
  - የወላጅ አማካሪው አካል ጉዳተኛ ልጅ ላላቸው ቤተሰቦችና ለት/ቤት ዲስትሪክቶች መረጃና ድጋፍ ይሰጣል። የወላጅ አማካሪው የዲስትሪክት ተቀጣሪ ሠራተኛ ሲሆን አካል ጉዳተኛ ልጅ ያለው ወላጅም ነው።
  - ለተጨማሪ መረጃ ____________________________________________ ያነጋግሩ።
- Ohio Coalition for the Education of Children with Disabilities (OCECD)
  - The OCECD ግዛት አቀፍ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ውስጥ ለሚኖሩ አካል ጉዳተኛ ጨቅላዎች፣ ሕጻናት፣ ልጆችና ወጣቶች ላሉባቸው ቤተሰቦችና አገልግሎት ለሚሰጧቸው አስተማሪዎችና ኤጄንሲዎች አገልግሎት ይሰጣል። የOCECD ፕሮግራሞች ወላጆች ለልጆቻቸው በሁሉም ትምህርታዊ ማዕቀፎች ውስጥ በመረጃ የተደገፉና ውጤታማ ተወካዮች እንዲሆኑ ያግዛሉ።
  - መረጃ ለማግኘት፣ ለ OCECD በስልክ ቁጥር (740) 382-5452 ወይም ቀጣዩን የ OCECD ድረ ገጽ ይጎብኙ፡www.ocecd.org።

## የቅድሚያ የቅሬታ አፈታት

የቅድሚያ የቅሬታ አፈታት ማለት ከት/ቤት ዲስትሪክት ጋር ያለዎትን ልዩነቶች ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድና ሌሎች የግጭት መፍቻ አማራጮችን መጠቀም ከመጀመርዎ በፊት ለመፍታት ጥረት ሲያደርጉ ማለት ነው። ከ Ohio Department of Education's Office for Exceptional Children የተመደበ ባለሙያ የልጅዎን ትምህርት በተመለከተ ጥያቄዎችዎንና አሳሳቢ ጉዳይዎን ለመፍታት የሚያግዝዎ ይሆናል።

The Ohio Department of Education የጽሑፍ ቅሬታ ወይም መደበኛ የዳኝነት ሒደቶችን የመሳሰሉ መደበኛ ሒደቶችን ከመጀመርዎ በፊት የቅድሚያ የግጭት አፈታትን ያበረታታል። ከ Ohio Department of Education's Office for Exceptional Children የተመደበ ባለሙያ የልጅዎን ትምህርት በተመለከተ ጥያቄዎችዎንና አሳሳቢ ጉዳይዎን ለመፍታት እንዲያግዝዎ ማነጋገር ይችላሉ። የቅድሚያ የቅሬታ አፈታትን በተመለከተ የሚያናግሩት ሰው ከፈለጉ፣ እባክዎ ዲፓርትመንቱን በቀጣዩ አድራሻ ያሳውቁ፡

- ስልክ ቁጥር፡ (614) 466-2650 ወይም ከክፍያ ነጻ (877) 644-6338; ወይም
- ኢሜይል፡ exceptionalchildren@education.ohio.gov።

## ፋሲሊቴሽን

በልጅዎ ላይ ለልዩ ትምህርት የሚደረግ ምዘና ወይም ዳግም ምዘና ወይም የልጅዎ ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ካሳሰበዎ፣ ፋሲሊቴሽን የሚባለው አማራጭ ሊጠቅምዎት ይችላል።

ፋሲሊቴሽን ማለት የልጅዎ ምዘና ወይም የ ቡድን (እርስዎምየዚህ ቡድን አባል ነዎት) ስብሰባ እንዲያመቻችልዎ ለዲፓርትመንቱ ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው። የት/ቤት ዲስትሪክቱም የልጅዎን ልዩ ትምህርት በተመለከተ ከእነዚህ ስብሰባዎች በአንዱ አመቻች እንዲመደብለት ለዲፓርትመንቱ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። እርስዎና ዲስትሪክቱ በስብሰባው ላይ አመቻች እንዲገኝ መስማማት አለባችሁ።

### የፋሲሊቴሽን ዓላማ

ፋሲሊቴሽን በቡድን ስብሰባ፣ ለምሳሌ በግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም ቡድን ስብሰባ፣ በምዘና ዕቅድ አወጣጥ ስብሰባ ወይም በምዘና ቡድን ስብሰባ ላይ ይካሄዳል። አመቻቹ የቡድኑ አባል ያልሆነና የቡድኑን ውሳኔ የማይወስን ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ነው። አመቻች መኖሩ ቡድኑ ውጤታማ እንዲሆንና በተማሪው ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲቆይ ያስችለዋል። አመቻቾች በልዩ ትምህርት ሒደቶች ላይ ከ Office for Exceptional Children ሥልጠና የተሰጣቸው ፕሮፌሽናል ሽምጋዮች ናቸው።

ፋሲሊቴሽን በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ። አንዴ ጥያቄውን ካቀረቡ፣ እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ ለመሳተፍ መስማማት አለባችሁ። ሁለታችሁም ከተስማማችሁ፣ Office for Exceptional Children ስብሰባውን የሚመራ አመቻች እንዲመርጡ ዕድል ይሰጥዎታል። እርስዎና ዲስትሪክቱ በአመቻ ላይ ካልተስማማችሁ፣ ጽ/ቤት ይመድብላችኋል። እርስዎም ሆኖ ዲስትሪክቱ ለፋሲሊቴሽን የምታወጡት ወጪ አይኖርም።

**አመቻች፡**



- ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ሆኖ ይቆያል (ለአንድ ወገን አያደላም ወይም ለእርስዎ ወይም ለዲስትሪክቱ ተጠሪ አይሆንም)፤
- ፕሮፌሽናል ሥልጠና የተሰጠው ***ገላጋይ*** ነው (ግጭቶችን ለመፍታት የሚያግዝ ብቃት ያለው ሰው ነው)፤
- የልዩ ትምህርት ሕጎች እና መስፈርቶችን በተመለከተ ሥልጠና እና ግንዛቤ አለው።
- የልጅዎ IEP ወይም የምዘና ቡድን አባል አይደለም፤
- ውሳኔ የማይሰጥ ቢሆንም ቡድኑ መፍትሔ እንዲፈልግ ይጠቀምበታል፤
- በእርስዎና በዲስትሪክቱ መካከል ውይይት እንዲጀመር ያግዛል፤
- ስብሰባው በአግባቡ እንዲካሄድ በማድረግ ሁሉም ሰው ሒደቱን እንዲያከብር ለማድረግ ያግዛል፤ እና
- ቡድኑ በልጅዎ እና በልጅዎ ፍላጎቶች ላይ እንዲያተኩር ያግዛል።

### ፋሲሊቴሽን በተመለከተ መታወስ ያለባቸው ቁልፍ ነጥቦች፡

- **ፋሲሊቴሽን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው።**
  - ወላጅና የት/ቤት ዲስትሪክቱ የሒደቱ አካል ለመሆን መስማማት አለባቸው። ወላጅና ዲስትሪክት በስብሰባው ላይ አመቻች እንዲገን ከተስማሙ፣ በስብሰባው ላይ ከዲስትሪክቱ ጋር መስማማት የለብዎትም ወይም የስብሰባውን አካሄድ በተመለከተ መስማማት አይጠበቅብዎትም። ወላጆች ምንጊዜም የራሳቸው አስተያየት እንዲኖራቸው ይፈቀድላቸዋል።
- **በፋሲሊቴሽን ስብሰባ ወቅት የተደረሰ ማንኛውም ስምምነት ባጠቃላይ ገዥ ነው። ይህም ማለት፣ ወላጅና የት/ቤት ዲስትሪክቱ የጋራ ውሳኔ ካሳለፉ በኋላ ስምምነቱን ማክበር አለባቸው ማለት ነው።**
  - ወላጅና ዲስትሪክቱ የልጅዎን ምዘና ወይም IEP በተመለከተ የሚፈርሙት ማንኛውም ሰነድ በሌላ ማንኛውም IEP ወይም የምዘና ቡድን ስብሰባ ላይ ከፈረሚቸው ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ ክብደት አለው።

ስለ ፋሲሊቴሽን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ the Ohio Department of Education ድረ ገጽ [education.ohio.gov](education.ohio.gov) በመጎብኘት ***ፋሲሊቴሽን***የሚለውን ይፈልጉ።

#### ፋሲሊቴሽን ለመጠየቅ

ዲስትሪክቱ በዚህ ሒደት ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆኑን ለማጣራት፣ የት/ቤት ዲስትሪክትዎን በቀጣዩ አድራሻ ያነጋግሩ ______________________________ ______________________________። ሁለቱም ወገኖች በፋሲሊቴሽን ውስጥ ለመሳተፍ አንዴ ከተስማሙ፣ እባክዎ ለ Ohio Department of Education's Office for Exceptional Children ያሳውቁ፡

- ስልክ ቁጥር፡ (614) 466-2650 ወይም ከክፍያ ነጻ (877) 644-6338; ወይም
- ኢሜይል፡ [exceptionalchildren@education.ohio.gov](mailto:exceptionalchildren@education.ohio.gov)።

## ግልግል



ግልግል ማለት ወላጆችና የት/ቤት ዲስትሪክቱ ገለልተኛና ሶስተኛ ወገን ባለሙያ በስብሰባ ላይ ተገኝቶ የአካል ጉዳተኛ ወይም አካል ጉዳት እንዳለበት ***የሚጠረጠር*** ተማሪን ትምህርት በተመለከተ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ሲስማሙ ነው። ሶስተኛ ወገን ማለት ይህ ግለሰብ፣ ማለትም ገላጋይ ለአንድ ወገን አያደላም ወይም ለወላጅ ወይም ለዲስትሪክቱ ተጠሪ አይሆንም፡ ፡ ግልግል ወላጆችና ዲስትሪክቶች የልጅዎን ልዩ ትምህርት በተመለከተ አለመስማማት በተፈጠረ ቁጥር የሚጠቀሙበት አንድ ምርጫ ነው።

### ግልግል ከክፍያ ነጻ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ ሊጠየቅ ይችላል

ግልግል በማንኛውም ጊዜ ሊጠየቅ ይችላል። ግልግል አንዴ ከተጠየቀ፣ እርስዎና የት/ ቤት ዲስትሪክቱ የሒደቱ አካል ለመሆን መስማማት አለባችሁ። ሁለታችሁም ለመሳተፍ ከተስማማችሁ፣ Office for Exceptional Children ስብሰባውን የሚመራ አመቻች እንድትመርጡ ዕድል ይሰጣችኋል። እርስዎና ዲስትሪክቱ በገላጋዩ ላይ ለመስማማት ካልቻላችሁ፣ OEC ይመድብላችኋል። ገላጋዩ የልጅዎን ልዩ ትምህርት በተመለከተ ያለውን ጉዳይ እንዴት መፍታት እንዳለባችሁ ገላጋዩ ሊነግራችሁ አይችልም። ከዚህ ይልቅ፣ ገላጋዩ ሁለቱም ወገኖች ልጅዎን በተመለከተ በአሳሳቢ ጉዳዮች ላይ እንድትወያዩና መፍትሔ እንድትፈልጉ ያግዛል።

መደበኛ ቅሬታ ለማቅረብ ወይም መደበኛ የዳኝነት ሂደት እንዲዘጋልጅዎ ከጠየቁ (ገጽ 17-25 ተመልከት)፣ the Ohio Department of Education የግልግል ሒደትን እንደ መጀመሪያ እርምጃ እንዲያስቡት ይጠይቅዎታል። እርስዎም ሆኖ ዲስትሪክቱ ለግልግል ሒደቱ የምታወጡት ወጪ አይኖርም።

## የግልግል ሒደት አጠቃላይ መግለጫ

### ግልግል መጠየቅ

እርስዎ ወይም የት/ቤት ዲስትሪክቱ በማንኛውም ወቅት ለ Ohio Department of Education የግልግል ጥያቄ ማቅረብ ትችላላችሁ። ቅሬታ ካቀረቡ ወይም የመደበኛ ዳኝነት ችሎት ከጠየቁ፣ ዲፓርትመንቱ ግልግልን በመጀመሪያ እርምጃነት ይጠቁማል። እርስዎም ሆኑ ዲስትሪክቱ ገላጋይ ለመጠቀም መስማማት አለባችሁ።

### ገላጋይ መምረጥ እና የስብሰባ ጊዜን ማቀድ

ገላጋዩ ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ነው። እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ በገላጋይ ላይ መስማማት አለባችሁ። ገላጋዩም በተቻለ ፍጥነት የስብሰባ ቀን መወሰን አለበት። የገላጋዩን ወጪ የሚሸፍነው ዲፓርትመንቱ ነው።

### የግልግል ስብሰባ

እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ አሳሳቢ ጉዳይዎን ይጋራሉ። ገላጋዩ ግጭቱን ፈትታችሁ የመጨረሻ የጽሑፍ ስምምነት ላይ እንድትደርሱ ያግዛችኋል፡፡ ባጠቃላይ፣ የተለየ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በግልግል ሒደቱ ወቅት የተነገረ ማንኛውም ነገር ከስብሰባው ውጪ ማጋራትም ሆነ በወደፊት የሕግ ነክ ሒደቶች ላይ መጠቀም አይቻልም።

### ስምምነት ላይ ከተደረሰ

የጽሑፍ ስምምነቱ ገዥ ሲሆን ወላጅና የት/ቤት ዲስትሪክቱም ይፈርሙበታል። ገዥ ማለት ወላጅና ት/ቤት ስምምነቱን ማክበር ያለባቸው ሲሆን ስምምነቱም በፍ/ቤት ይጸናል።

### ስምምነት ላይ ካልተደረሰ

በግልግል ስምምነት ላይ ካልተደረሰና እርስዎም ለግዛቱ ቅሬታ ካቀረቡ፣ Office for Exceptional Children ቅሬታውን ይፈታል። በግልግል ስምምነት ላይ ካልተደረሰና እርስዎም መደበኛ ዳኝነት ከጠየቁ፣ ቀጣዩ ሒደት መደበኛ ዳኝነት ይሆናል።



**ገላጋዩ፡**

- ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ሆኖ ይቆያል (ለአንድ ወገን አያደላም ወይም ለእርስዎ ወይም ለዲስትሪክቱ ተጠሪ አይሆንም)፤
- ውሳኔ እንዲሰጥ አይፈቀድለትም። ከዚህ ይልቅ፣ ገላጋዩ እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ የልጅዎን ትምህርት የሚመለከተውን ጉዳይ እንዲፈቱ ያግዛል፤
- እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ በጽሑፍ የግልግል ስምምነት ላይ ለመወሰን ከእርስዎና ከት/ቤት ዲስትሪክት ጋር አብሮ ይሰራል፤
- የግልግል ስብሰባው በአግባቡ እንዲካሄድ በማድረግ ሁሉም ሰው ሒደቱን እንዲያከብር ለማድረግ ያግዛል፤
- ሁሉም ሰው በልጅዎ እና በልጅዎ ፍላጎቶች ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል፤
- በእርስዎና በት/ቤት ዲስትሪክቱ መካከል ውይይት እንዲጀመር ያግዛል።

## ግልግልን በተመለከተ መታወስ ያለባቸው ቁልፍ ነጥቦች

- **ግልግል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው።**
  - ወላጅና የት/ቤት ዲስትሪክቱ የሒደቱ አካል ለመሆን መስማማት አለባቸው። ወላጅና ዲስትሪክት በግልግል ውስጥ ለመሳተፍ ከተስማሙ፣ በስብሰባው ላይ ከዲስትሪክቱ ጋር መስማማት የለብዎትም ወይም የስብሰባውን አካሄድ በተመለከተ መስማማት አይጠበቅብዎትም።
- **ግልግል ሚስጥራዊ ነው።**
  - በግልግል ስብሰባ ወቅት የተነገረ ማንኛውም ጉዳይ ሚስጥራዊ (ግላዊ) ሆኖ የሚቆይ ሲሆን ልዩ ሁኔታ ከሌለ በስተቀርም በሌላ ጊዜ ጥቅም ላይ መዋል አይችልም።
- **በግልግል ወቅት የተፈረመ ማንኛውም የጽሑፍ ስምምነት ባጠቃላይ ገዥ ነው። ይህም ማለት፣ ወላጅ እና የት/ቤት ዲስትሪክቱ የጋራ ውሳኔ ካሳለፉ በኋላ የጽሑፍ ስምምነቱን ማክበር አለባቸው ማለት ነው።**
  - ወላጅና ዲስትሪክቱ የልጅዎን ምዘና ወይም IEP በተመለከተ የሚፈርሙት ማንኛውም ሰነድ በሌላ ማንኛውም IEP ወይም የምዘና ቡድን ስብሰባ ላይ ከፈረሟቸው ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ ክብደት አለው።

### ግልግል ለመጠየቅ

ዲስትሪክቱ በዚህ ሒደት ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆኑን ለማጣራት፣ የት/ቤት ዲስትሪክትዎን የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር በቀጥታ አድራሻ ያነጋግሩ ______________________________ ________________________________። ሁለቱም ወገኖች በግልግል ውስጥ ለመሳተፍ አንዴ ከተስማሙ፣ እባክዎ ለ Ohio Department of Education's Office for Exceptional Children ያሳውቁ፡

- ስልክ ቁጥር፡ (614) 466-2650 ወይም ከክፍያ ነጻ (877) 644-6338; ወይም
- ኢሜይል፡ **exceptionalchildren@education.ohio.gov**።



## የግዛት ቅሬታ ማቅረብ

የልጅዎን ልዩ ትምህርት በተመለከተ አሳሳቢ ጉዳይ ካለዎት ሌላው ያለዎት አማራጭ በት/ቤት ዲስትሪክቱ ወይም በሌላ መንግስታዊ ኤጀንሲ ላይ መደበኛ የግዛት አቀፍ ቅሬታ በማቅረብ ይህን ቅሬታም ለ Ohio Department of Education's Office for Exceptional Children ማስገባት ነው።

### የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ የሚወጣ ወጪ የለም

የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ የሚወጣ ወጪ የለም የግዛት ቅሬታ አፈታት ሒደት ባጠቃላይ ከመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ችሎት በፈጠነ ሁኔታ ለችግር መፍትሔ የሚሰጥ ሲሆን ከመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ያነሰ የተቀናቃኝነት (ወይም ፍጥጫ) ስሜት አለው። የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ፣ የተፈረመና በጽሑፍ የተዘጋጀ ቅሬታዎን (ኦሪጂናል) ለ መላክ ያለብዎት ሲሆን የቅሬታውን ***ኮፒ*** ም በቀጥታ ለት/ቤት ዲስትሪክት መላክ አለብዎት።

በቅሬታዎ ውስጥም ተጥሰዋል የሚሏቸውን የፌዴራል ወይም የግዛት የልዩ ትምህርት መስፈርቶች (የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ደንብ ወይም ኦሃዮ የአካል ጉዳተኛ ሕጻናት ትምህርት የአሰራር መስፈርቶች ጥሰት) መግለጽ አለበት። ቅሬታው የአንድን ሕግ ስም ወይም ድንጋጌ መጥቀስ የማይጠበቅበት ቢሆንም የልዩ ትምህርት መስፈርትን ይጥሳል ብለው የሚያምኑበትና ግዛቱ የወሰደውን ወይም ያልወሰደውን እርምጃ መጥቀስ አለበት። በተጨማሪም፣ ዲስትሪክትዎ የልዩ ትምህርት መስፈርትን ጥሷል ብለው ያሰቡበትን ምክንያት የሚደግፉ እውነታዎችንም በቅሬታዎት ውስጥ ማካተት አለብዎት።

### የግዛት ቅሬታዎች ክለሳ

The Office for Exceptional Children በአግባቡ የቀረበ ቅሬታን ተመልክቶ እንዳስፈላጊነቱም የሚመረምር ሲሆን የት/ቤት ዲስትሪክቱ ከልጅዎ ትምህርት ጋር የተያያዘ የልዩ ትምህርት መስፈርትን መጣስ አለመጣሱን ይወስናል። በተጨማሪም፣ ሶስተኛ ወገን፣ ማለትም ከእርስዎ ውጭ ያለ ሰው ወይም ከት/ቤት ዲስትሪክቱ ውጭ ያለ ኤጄንሲ ወይም ድርጅት ዲስትሪክቱ ተማሪን የሚመለከት የልዩ ትምህርት መስፈርትን እንደጣሰ ካመነ ለዲፓርትመንቱ የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ ይችላል።

የልዩ ትምህርት ጥሰት ተፈጸመ ከተባለበት ቀን አንስቶ በ ***አንድ ዓመት*** ውስጥ የግዛት ቅሬታ ለዲፓርትመንቱ መቅረብ አለበት። ቅሬታ ከመቅረቡ በፊት ከአንድ ዓመት በላይ በሆነ ጊዜ የተፈጸመ የደንብ ጥሰትን የሚመለከት ማንኛውም ቅሬታ ምርመራ አይደረግበትም/መፍትሔ አይሰጠውም።

### መደበኛ የግዛት ቅሬታ የሚቀርብበት መንገድ

ልዩ ትምህርትን በተመለከተ መደበኛ የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ ከፈለጉ፡

- የግዛት **ቅሬታ ማቅረቢያ** ቅጽ ሞልተው ለ Ohio Department of Education's Office for Exceptional Children ይላኩት፤ ወይም
- የቅሬታ ደብዳቤ መጻፍ፤ ወይም
- ለዲፓርትመንቱ ሠራተኞች በስልክ ቁጥር 1-877-644-6338 በመደወል የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ይጠይቁና ቅጹን ሞልተው ለዲፓርትመንቱ ይመልሱ።



### ቅሬታዎን ለማን ይልካሉ

ቅሬታዎን መላክ ያለብዎ **ለ** Ohio Department of Education's Office for Exceptional Children and እና ለት/ቤት ዲስትሪክቱ ዋና ተቆጣጣሪ ነው።

ኦሪጂናል ቅሬታውን የሚልኩበት አድራሻ፡

The Ohio Department of Education
Office for Exceptional Children
Attn: የግጭት አፈታት ክፍል ረዳት ዳይሬክተር
25 South Front Street
Mail Stop 409
Columbus, Ohio 43215-4183

### ለጊዜው ማዘግየት

ለጊዜው ማዘግየት ማለት በግዛት ቅሬታ ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን ለጊዜው ማቆም ማለት ነው፡ ፡ እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ውስጥ ተሳታፊ ከሆናችሁና እርስዎ ወይም ዲስትሪክቱ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የግዛት ቅሬታ ካቀረባችሁ፣ the Ohio Department of Education የግዛት ቅሬታውን ለጊዜው ያቆመዋል። በሌላ አነጋገር፣ ዲፓርትመንቱ መደበኛ የዳኝነት ስርዓቱ እስከሚጠናቀቅና የግዛት ቅሬታዎ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ ይጠብቃል፡ ፡ የመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ጥያቄዎን ከተዉ፣ ዲፓርትመንቱ የግዛት ቅሬታውን ካስቆመበት በማስቀጠል ቅሬታዎን ወደመፍታት ያመራል።

የመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ከተካሄደና ገለልተኛ የሆነ የችሎት መኮንን ውሳኔ ከሰጠ፣ ዲፓርትመንቱ የግዛት ቅሬታውን ካስቆመበት የሚያስቀጥለው በችሎት መኮንኑ ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በቅሬታዎ ውስጥ ካሉ ብቻ ነው።



**በግዛት ቅሬታ ውስጥ ሊያካትቱ የሚገባዎት ነጥቦች ዝርዝር**

- **የት/ቤት ዲስትሪክቱ የፌዴራል ወይም የግዛት የልዩ ትምህርት መስፈርትን ጥሷል የሚል ሐተታ።**
- **የችግሩ መግለጫ፣ የቅሬታዎ መነሻ የሆነዎትን እውነታዎች ጨምሮ።**
- **የመገኛ መረጃዎና ኦሪጂናል ፊርማዎ።**
- **አንድን ተማሪ በተመለከተ የልዩ ትምህርት ጥሰት ተፈጽሟል የሚሉ ከሆነ፡**
  - የተማሪው ስምና መኖሪያ አድራሻ፤
  - ተማሪው የሚማርበት ት/ቤት ስም፤
  - ቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት ከሆነ (በ McKinney-Vento Homeless Assistance Act እንደተገለጸው) ተማሪውን የሚመለከት የግንኙነት መረጃ ተማሪው የሚማርበት ት/ቤት ስም
  - ከችግሩ ጋር የተያያዙ እውነታዎችን ጨምሮ የችግሩ ዓይነት መግለጫ፤ እና
  - ቅሬታው በቀረበበት ወቅት ቅሬታ አቅራቢው እስከሚያውቀውና እስካገኘው ድረስ ለችግሩ በመፍትሔነት የተጠቆመው ጉዳይ።
- ***ቅሬታው ላይ ኦሪጂናል ፊርማዎት ማረፍ ስላለበት ቅሬታውን በፋክስ ወይም በኢሜይል መላክ አይችሉም።***
- **ስም አልባ ቅሬታዎች ተቀባይነት የላቸውም።**

## የግዛት ቅሬታ አቀራረብ ሒደት

ዲፓርትመንቱ የግዛት ቅሬታዎን ሲቀበል፣ ቅሬታው በአግባቡ እስከቀረበ ድረስ ክለሳውን በመጀመር እንዳስፈላጊነቱም በልዩ ትምህርት መስፈርቶች ላይ ተፈጸመ የተባለውን ጥሰት(ቶች) ይመረምራል። The Office for Exceptional Children ቅሬታዎን በተቀበለ በ60 መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው መፍትሔ መስጠት አለበት።

the Office for Exceptional Children የቅሬታ አፈታት ሒደት አካል አድርጎ፡

- ቅሬታዎን በመመልከት በቅሬታዎ ውስጥ የተጠቀሱ ውንጀላዎችን የመፍታት ስልጣን ያለው መሆኑን ይወስናል፤
- መፍትሔ የሚሰጣቸውን ቅንጀላዎች፣ ምርመራውን ጨምሮ (አስፈላጊ ከሆነ) በጽሑፍ ለእርስዎና ለት/ቤት ዲስትሪክቱ ያሳውቃል፤
- ግልግል ወይም ፋሲሊቴሽን ለእርስዎና ለዲስትሪክቱ እንደ አማራጭ የቅሬታ መፍቻ ዘዴ ይጠቁማል፤
- በቅሬታዎ ውስጥ ያሉ ውንጀላዎችን በተመለከተ ከእርስዎና ከዲስትሪክቱ የሚፈልገውን ተጨማሪ መረጃ ይጠይቃል፤
- እርስዎና ዲስትሪክቱ ያቀረባችኋቸውን ተጨማሪ ሰነዶችና መረጃዎች ይመለከታል፣ የስልክ ቃለ መጠይቅ ያደርጋል፣ እንዳስፈላጊነቱም የልጅዎን ዲስትሪክት ይጎበኛል፤
- ዲስትሪክትዎ እርስዎ ላቀረቡት ቅሬታ መልስ እንዲሰጥ እድል በመስጠት መፍትሔ ይተቁማል፤ እና
- የልዩ ትምህርት ጥሰት መፈጸም አለመፈጸሙን በተመለከተ ውሳኔውን ለእርስዎም ሆነ ለዲስትሪክቱ በደብዳቤ ያሳውቃል (ቅኝትና ምርመራ ካደረገ በኋላ፣ ቅሬታዎን ከተቀበለ በኋላ ከ60 ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ)።

### የጊዜ ገደብ ማራዘሚያዎች

የጊዜ ማራዘሚያ ካለ፣ ዲፓርትመንቱ ለቅሬታው መፍትሔ በመስጠት የውሳኔ ደብዳቤውን ለማሳወቅ ከ60 ቀናት በላይ ሊኖረው ይችላል። የግዛት ቅሬታን ለመፍታት የ60 ቀናት የጊዜ ገደብ ሊራዘም የሚችለው፡

- እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ ጉዳዩን በግልግል፣ በፋሲሊቴሽን ወይም በሌላ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ ለመፍታት እንዲሞክሩ ተጨማሪ ጊዜ ለማግኘት ስትስማሙ፤ ወይም
- ልዩ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ወቅት እንደየሁኔታው (በOffice for Exceptional Children በሚወሰነው መሰረት)።

### ትክክለኛ ያልሆነ ቅሬታ አቀራረብ

መፍትሔ እንዲያገኝ የሚፈልጉትን ጉዳይ በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በሙሉ ባለማካተትዎ ምክንያት Office for Exceptional Children የግዛት ቅሬታን በአግባቡ አላቀረቡም ብሎ ከወሰነ፣ ወይም Office for Exceptional Children ቅሬታውን የመመርመር ሥልጣን ከሌለው፣ Office for Exceptional Children የሚከተለውን ጉዳይ የሚያስረዳ ደብዳቤ ይልክልዎታል፡ ቅሬታዎን የመፍታት ሒደቱን ለምን እንደማያስቀጥል፣ የዚህን ውሳኔ ምክንያትና፣ አግባብነት ካለው፣ በአግባቡ የቀረበ ቅሬታ ተብሎ እንዲቆጠር በአዲሱ ቅሬታዎ ውስጥ ማካተት ያለብዎትን መረጃ።

### ቅሬታን ድጋሚ ማቅረብ

ቅሬታዎትን ከአዲስ መረጃ ጋር ማቅረብ ካለብዎት፣ የልዩ ትምህርት ጥሰቱ ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ውስጥ ቅሬታዎን ለ Ohio Department of Education እና ለት/ቤት ዲስትሪክት መላክዎን ያረጋግጡ። ዲፓርትመንቱ መርምሮ የመወሰን ሥልጣን የሌለባቸውን ጉዳዮች በቅሬታዎ ውስጥ ካካተቱ፣ እንዳግባብነቱ ይህን ጉዳይ ለመፍታት ወደሚችሉ አካላት ያስተላልፍዎታል።

**ቅሬታ ማቅረብ**

- ጥሰቱ በተፈጸመ በአንድ ዓመት ውስጥ ቅሬታ ይቀርባል።
- ወላጅ ኦሪጂናሉን ለ Ohio Department of Education እና ኮፒውን ለዲስትሪክት ይሰጣል።
- ቅሬታው ተፈጸሙ የተባሉ የልዩ ትምህርት መስፈርቶችን ከደጋፊ እውነታዎች ጋር ያቀርባል።

**የ Ohio Department of Education ቅሬታን ይመለከታል**

- ዲፓርትመንቱ ቅሬታ ላስገባው ግለሰብ ለት/ቤት ዲትሪክቱ የማረጋገጫ ደብዳቤ ይልካል።
- ቅሬታው በአግባቡ ካልቀረበ ወይም ዲፓርትመንቱ ይህን ጉዳይ ለመፍታት ሥልጣን ከሌለው የOhio Department of Education ይህንኑ የሚገልጽ ደብዳቤ ይልካል።

**አፈታት**

- ዲፓርትመንቱ ሁሉንም ሰነዶች መርምሮ እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ ሰነድ/መረጃ ይጠይቃል።
- ዲፓርትመንቱ እንዳስፈላጊነቱ አግባብነት ያላቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ ያደርጋል።

**ዲፓርትመንቱ የግኝቶችን ደብዳቤ ይልካል**

- ዲፓርትመንቱ እያንዳንዱን ክስ በተመለከተና የልዩ ትምህርት ጥሰት ስለመፈጸሙ ይወስናል።
- ዲስትሪክቱ ጥሰት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ዲፓርትመንቱ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል።



## የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ማቅረብ

ወላጆች የልጃቸውን ልዩ ትምህርት በተመለከተ የሚያሳስቧቸውን የተወሰኑ ጉዳዮች ከት/ቤት ዲስትሪክታቸው ጋር ሊፈቱ ከሚችሉባቸው መንገዶች አንዱ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት እንዲሞቻች ለዲስትሪክቱ ቀጥተኛ ጥያቄ በማቅረብና ኮፒውንም ለ Ohio Department of Education መላክ ነው። ይህን ካደረጉ፣ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ (የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት መጠየቂያም ይባላል) አቀረቡ ማለት ነው። የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉ ሌሎች አካላትም አሉ፡



- ዕድሜው ቢያንስ 18 ዓመት የሞላው ተማሪ፤
- የት/ቤት ዲስትሪክት፤ ወይም
- ሌሎች መንግስታዊ የትምህርት ኤጄንሲዎች።

### ቅሬታ የማቅረቢያ ምክንያቶች

የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው የልጅዎን ልዩ ትምህርት የሚከተሉትን መስኮች በተመለከተ ነው፡

- አካል ጉዳተኛ ሕጻንን መለየት፤
- አካል ጉዳተኛ ሕጻንን መመዘን፤
- የአካል ጉዳተኛ ሕጻን ትምህርታዊ ምደባ፤ ወይም
- ለልጅዎ ከክፍያ ነጻና አግባብነት ያለው የመንግስት ትምህርት (FAPE) መስጠት።

የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታው የፌዴራል ወይም የግዛት የልዩ ትምህርት መስፈርቶች መጣሳቸውን መጥቀስ ያለበት ሲሆን ወላጅ (ወይም ቅሬታ ያቀረበው መንግስታዊ የትምህርት ኤጄንሲ) ተፈጽሟል ስለተባለው የልዩ ትምህርት ጥሰት ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን አንስቶ በ ***ሁለት ዓመታት*** ውስጥ መቅረብ አለበት። የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታው ለOhio Department of Education ሲደርሰው የሚመለከታቸው ወላጆች እና የት/ቤት ዲስትሪክቱ በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት የመሳተፍ ምርጫ ሊኖራቸው ይገባል። የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት መደበኛ ስነ-ስርዓት ሲሆን ዲፓርትመንቱም የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታውን ለመፍታት ችሎት የሚያካሂድ ገለልተኛ የችሎት መኮንን ይመድባል።

### መካተት ያለበት መረጃ

ዲፓርትመንቱ መደበኛ የዳኝነት ስርዓት ለመጠየቅ የሚያገለግል ቅጽ ያቀርባል። ጥያቄውን የሚያቀርበው ግለሰብ ወይም መንግስታዊ የትምህርት ኤጄንሲ **[የዲፓርትመንቱን ቅጽ]** እንዲጠቀም የማይገደድ ቢሆንም ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ በሚያቀርብበት ወቅት ይህን ተፈላጊ መረጃ ማቅረብ አለበት፡

1. የተማሪው ስም፤
2. የተማሪው አድራሻ ወይም የመገኛ መረጃ፤
3. የት/ቤት ዲስትሪክቱ ስም፤
4. ልጅዎ ቤት አልባ ከሆነ፣ ልጅዎን በተመለከተ ያለ የመገኛ አድራሻ እና ልጅዎ የሚማርበት ት/ቤት ስም፤
5. ልጅዎን የሚመለከት የተወሰነ ችግር፣ እንደዚሁም ችግሩን የሚመለከቱ እውነታዎች መግለጫ፤ እና
6. ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ ሃሳቦች ወይም አስተያየቶች።

የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ከግዛት ቅሬታ ጋር ተመሳሳይ የሆነና ዝርዝር መረጃ መያዝ ያለበት ሲሆን (ገጽ 18 ተመልከት)፣ ኦሪጂናል ፊርማ ግን አያስፈልግም፡ ፡ ለት/ቤት ዲስትሪክቱና ለዲፓርትመንቱ በአካል፣ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በኢሜል ሊላክ ይችላል። መጀመሪያ ባቀረቡት የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ውስጥ ያልተካተቱ ጉዳዮች በመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ወቅት በችሎት መኮንኑ አይመረመሩም።

### የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታን ማሻሻል

የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታን ማሻሻል ማለት ቅሬታው ለ ከቀረበ በኋላ ማሻሻያ ማድረግ ማለት ነው። የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታዎን ማሻሻል የሚችሉት፡

- ሌላኛው ወገን የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬው እንዲሻሻል መስማማቱን በጽሑፍ ሲያረጋግጥና ቅሬታውን በመፍትሔ ስብሰባ አማካይነት ለመፍታት ዕድል ከተሰጠው (የመፍትሔ ስብሰባ ምንነት በ ገጽ 23) ላይ ተገልጿል)፤ ወይም
- ገለልተኛው የችሎት መኮንን ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ነው። የችሎት መኮንኑ ይህን ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው መደበኛ የዳኝነት ስርዓት ከመጀመሩ አምስት ቀናት በፊት እንጂ ከዚያ በኋላ መሆን የለበትም።

## የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት የጊዜ ሰሌዳና ሒደት

መደበኛ የዳኝነት ስርዓት ቅሬታ የሚያቀርቡት የልጅዎ ት/ቤት ዲስትሪክት ላይ ከሆነ፣ ዲስትሪክቱ አስቀድሞ ያልሰጠዎት ካልሆነ በስተቀር የእርስዎ ቅሬታ በደረሰው በ10 የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ተጣሰ የተባለውን ልዩ ትምህርት በተመለከተ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ወይም ምላሽ ሊሰጥዎት ይገባል (ገጽ 9ን ተመልከት)። ዲስትሪክቱ የሚሰጥዎት የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ማካተት ያለበት፡

- እርስዎ የጠየቁትን እርምጃ ወይም ቅሬታው የሚያተኩርበትን ጉዳይ የሚመለከት መግለጫ። ይህ እርምጃም ዲስትሪክቱ ሊወስድ የፈለገው ወይም አልወስድም ያለው እርምጃ ሊሆን ይችላል። ዲስትሪክቱም በምላሹ ላይ ት/ቤቱ እርምጃ ለመውሰድ የፈለገበትን ወይም አልወስድም ያለበትን ምክንያት ማስረዳት አለበት።
- ልጅዎን ለመመዘን የተጠቀማቸውን ዘዴዎች፣ ልጅዎን የሚመለከቱ ማስረጃዎችና ዲስትሪክቱ እርምጃ ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ ውሳኔው የተጠቀማቸውን ሪፖርቶች በሙሉ መግለጽ፤
- የIEP ቡድን ለልጅዎ ታሳቢ ያደረጋቸውንን ሌሎች ምርጫዎችና እነዚያን ምርቻዎች ውድቅ ያደረገባቸው ምክንያቶች መግለጫ፤ እና
- ዲስትሪክቱ እርምጃ ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ ከወሰነው ውሳኔ ጋር አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ነጥቦች መግለጫ።

የት/ቤት ዲስትሪክቱ እርስዎ ማግኘት ስለሚችሏቸው በነጻ ወይም በአነስተኛ ክፍያ ስለሚቀርቡ የሕግ ድጋፎችና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች መረጃ ሊሰጥዎት ይገባል።

እርስዎ ወላጅ በመሆንዎት የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ከቀረበብዎ፣ በ10 የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው መልስ መስጠት አለብዎ። ምላሽዎም በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በተለይ የሚሸፍን መሆን አለበት።

### ምሉዕነት

ሌላኛው ወገን ለገለልተኛ የችሎት መኮንኑና ቅሬታውን ላቀረበው ወገን ቅሬታው መስፈርቶቹን አያሟላም የሚል ማሳወቂያ ካልሰጠ (የተሟላ አይደለም) ***በስተቀር*** የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ የተሟላ ነው (በአግባቡ የቀረበ ነው) ተብሎ ይቆጠራል። ሌላኛው ወገን የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታን ምሉዕነት መገዳደር አለበት።

ለምሳሌ፣ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ለዲስትሪክትዎ ካቀረቡ (ኮፒውንም ለOhio Department of Education ካስተላለፉ) ዲስትሪክቱ ቅሬታው በአግባቡ የቀረበ ነው ብሎ እንደማያስብ በ15 ቀናት ውስጥ ለችሎት መኮንኑ በጽሑፍ ካላሳወቀ በስተቀር ቅሬታው የተሟላ ተደርጎ ይቆጠራል። ከዚያም፣ የችሎት መኮንኑ የዲስትሪክትዎ የጽሑፍ ማሳወቂያ በደረሰው በአምስት የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታዎ የተሟላ መሆኑን (በገጽ 21 ላይ የተገለጹትን የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ መስፈርቶች ማሟላቱን) መወሰን አለበት። የችሎት መኮንኑ በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ለእርስዎና ለዲስትሪክቱ መላክ አለበት።

የችሎት መኮንኑ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታዎ የተሟላ አይደለም ብሎ ከወሰነ፣ አዲስ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ የማቅረብ ወይም የመጀመሪያውን የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ የማሻሻል አማራጭ ያለዎት ሲሆን ዲስትሪክቱም ስምምነቱን መግለጽና ጉዳዩን በመፍትሔ ስብሰባ በኩል የመፍታት አማራጭ የቀረበለት ሊሆን ይገባል ወይም የችሎት መኮንኑ ችሎቱ ከመጀመሩ ከአምስት ቀናት በፊት ፈቃድ መስጠት አለበት።

የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታዎን በአግባቡ ካሻሻሉ፣ የ30 ቀናት የመፍትሔ ጊዜ (ገጽ 23 ተመልከት) የሚጀምረው የማሻሻያ ቅሬታ ሲያስገቡ ነው።

## የመደበኛ ዳኝነት ስነ-ስርዓት አፈታት

### የመፍትሔ ጊዜ

የመፍትሔ ጊዜ ማለት የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ በቀረበበትና መደበኛ የዳኝነት ችሎቱ በሚካሄድበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ ነው። የመፍትሔ ጊዜው ውስጥ የመፍትሔ ስብሰባ የሚካሄድ ሲሆን ይህ ደግሞ ችሎቱ በይፋ ከመጀመሩ በፊት የልዩ ትምህርት አለመግባባትን ለመፍታት የሚያስችል ዕድል ይሰጣል፡ ፡ የመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ቅሬታ አቅርበው በመፍትሔ ሒደቱ ውስጥ ሳይሳተፉ ቢቀሩ፣ የመደበኛ የዳኝነት ስርዓትን ጊዜ ሰሌዳ ያዘገየዋል (የጊዜ ሰሌዳን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ከታች ቀርቧል)።

የመፍትሔ ጊዜው የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታው ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ (ወይም ቅሬታው በአግባቡ ከተሻሻለበት ቀን አንስቶ) 30 ቀናት ነው። የት/ቤት ዲስትሪክቱ በ30 ቀናት ውስጥ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታውን ለእርስዎ በሚያረካ መልኩ መፍትሔ ካልሰጠ፣ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ሊቀጥል ይችላል። እርስዎና ዲስትሪክቱ ከ30 ቀናት በላይ የሚወስድ ግልግል ላይ ለመሳተፍ ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ የ30 ቀናት ጊዜው አንዴ ካለፈ፣ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ለማካሄድ ወይም ገለልተኛው የችሎት መኮንን ውሳኔ ለመስጠት የ45 ቀናት የጊዜ ሰሌዳ ይኖራል (ገጽ 24 ተመልከት)። በእነዚህ 30 ቀናት ውስጥ እርስዎና ዲስትሪክቱ ስምምነት ለማድረግ አለመቻላችሁን በጽሑፍ ከገለጻችሁ የ30 ቀናት የመፍትሔ ጊዜው አስቀድሞ የሚያበቃ እንደሚሆን ያስተውሉ።

የት/ቤት ዲስትሪክቱ በ30 ቀናት የመፍትሔ ጊዜ ውስጥና የመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ቅሬታ በደረሰው በመጀመሪያዎቹ 15 የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሔ ስብሰባ የጊዜ ሰሌዳን መወሰን አለበት። ዲስትሪክቱ በ15 የመቁጠሪያ ውስጥ የመፍትሔ ስብሰባ ካላደረገ ወይም በመፍትሔ ስብሰባ ላይ ካልተሳተፈ፣ የችሎት መኮንኑ የ45 ቀናት የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት የጊዜ ሰሌዳ እንዲጀምር መጠየቅ ይችላሉ። ዲስትሪክቱ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ካቀረበ የመፍትሄ ስብሰባ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት አይጠበቅበትም።

### የመፍትሔ ስብሰባ

የመፍትሔ ስብሰባው ዓላማ በቅሬታዎ ውስጥ የተጠቀሱ ችግሮችን ለመወያየትና የት/ቤት ዲስትሪክቱም ከእርስዎ ጋር በመስራት ወደ መፍትሔ የሚደርስበት እድል እንዲያገኝ ለማስቻል ነው። የመፍትሔ ስብሰባውን የመጥራት ኃላፊነቱ የዲስትሪክቱ ሲሆን እርስዎም መሳተፍ አለብዎት። በመፍትሔ ስብሰባው ላይ ካልተሳተፉና በዲስትሪክት ሰነዶች ላይም የእርስዎ ተሳትፎ ከሌለ፣ ዲስትሪክቱ የ30 ቀናት ጊዜው ሲጠናቀቅ የችሎት መኮንኑ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታዎን ውድቅ እንዲያደርግ መጠየቅ ይችላል።

በመፍትሔ ስብሰባው ላይ መሳተፍ የሚችሉት የ IEP ቡድን አባላት እነማን እንደሆኑ የምትወስኑት እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ ናችሁ። በዚህ ስብሰባ ላይ የት/ቤት ዲስትሪክቱ ተወካይ መሳተፍ ያለበት ሲሆን እርሱም ዲስትሪክቱን ወክሎ ውሳኔ መወሰን የሚችል ነው።

እርስዎ ጠበቃዎ እንዲገኝ ካልፈለጉ በስተቀር የዲስትሪክቱም ጠበቃ በስብሰባው ላይ አይሳተፍም። እርስዎና ዲስትሪክቱ የመፍትሔ ስብሰባው እንዲቀር የጽሑፍ ስምምነት ካላደረጋችሁ ወይም ከመፍትሔ ስብሰባ ይልቅ ግልግል ለመጠቀም ካልተስማማችሁ በስተቀር ይህ ስብሰባ በመፍትሔው ሒደት ውስጥ ወሳኝ ደረጃ ነው። እርስዎና ዲስትሪክቱ ከተስማማችሁ የ30 ቀናት ጊዜው ቢያልፍም ግልግል ለማካሄድ ይፈቀድላችኋል። ይህም የ45 ቀናት የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎትና የውሳኔ መስጫ የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጀምር ያደርጋል።

እርስዎና ዲስትሪክቱ አለመግባባታችሁን በመፍትሔ ስብሰባው ከፈታችሁ፣ ሁለታችሁም የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሕጋዊ ስምምነት መፈረም አለባችሁ፡

- አሁን ምን እንደሚከሰት በጽሑፍ የሚገልጽ፤
- በእርስዎና በዲስትሪክት ተወካዩ የተፈረመ፤ እና
- በፍ/ቤት ተፈጻሚ ሊሆን የሚችል።

ሕጋዊነት ያለው ማለት እርስዎ ወይም የት/ቤት ዲስትሪክቱ ስምምነቱን ካላከበራችሁ ፍ/ቤት እርስዎ ወይም ዲስትሪክቱ እንድታከብሩት ሊያደርግ ይችላል ማለት ነው።

እርስዎ ወይም የት/ቤት ዲስትሪክቱ ላለመስማማት ከወሰናችሁ፣ ስምምነቱን ከፈረማችሁ በኋላ ከሁለት አንዳችሁ ስምምነቱ በተፈረመ በሶስት ስራ ቀናት ውስጥ መሰረዝ ትችላላችሁ።

እርስዎ እና የት/ቤት ዲስትሪክቱ የ30 ቀናት የመፍትሔ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት የመደበኛ ዳኝነት ስነ-ስርዓት ቅሬታን በተመለከተ ስምምነት ላይ ከደረሳችሁ፣ ቅሬታው የሚዘጋ ሲሆን የመደበኛ ዳኝነት ችሎትም አይኖርም።

## የችሎቱ ሒደት

የመደበኛ ዳኝነት ስነ-ስርዓት ችሎት መታቀድና መካሄድ ያለበት ለእርስዎና ለት/ቤት ዲስትሪክቱ አመቺ በሆነ ቦታና ጊዜ ነው። ገለልተኛው የችሎት መኮንን በችሎቱ ወቅት መረጃ መተላለፍ ሲኖርበት ለእርስዎና ለዲስትሪክቱ በተመሳሳይ ጊዜ ያሳውቃል። በሌላ አነጋገር፣ በገለልተኛ የችሎት መኮንን፣ በእርስዎ እና በዲስትሪክቱ መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በጋራ እንጂ በተናጠል መካሄድ የለበትም።

የ45 ቀናት የመደበኛ ዳኝነት ስነ-ስርዓት የጊዜ ሰሌዳ (ለገለልተኛ የችሎት መኮንኑ ውሳኔ መስጫ) የሚጀምረው የ30 ቀናት የመፍትሔ ጊዜ ሲጠናቀቅ ወይም ከሚከተሉት መካከል አንዱ ከተከሰተ በኋላ ነው፡

- እርስዎና ዲስትሪክቱ የመፍትሔ ስብሰባው እንዲቀር በጽሑፍ ስምምነት ካደረጋችሁ፤ ወይም
- ጉዳዮቹን በመፍትሄ ስብሰባ ወይም በግልግል ስብሰባ ወቅት መወያየት ከጀመራችሁ፣ እርስዎና ዲስትሪክቱ ስምምነት ላይ መድረስ እንዳልተቻለ በጽሑፍ መስማማት አለባችሁ።
- እርስዎና ዲስትሪክቱ ወደ ግልግል ሒደት ለመቀጠል እንድትችሉ ከ30 ቀናት የመፍትሔ ጊዜ በላይ ለመቆየት በጽሑፍ ከተስማማችሁ፣ እርስዎ ወይም ዲስትሪክቱ ከግልግል ሒደቱ መውጣት ትችላላችሁ።

ገለልተኛው የችሎት መኮንን በ45 ቀናት የችሎት የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከአንዱ ወገን በሚቀርብለት ጥያቄ ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት (ወይም ማራዘሚያ ለመፍቀድ) ካልወሰነ በስተቀር የሚከተሉት ሁኔታዎች ይከናወናሉ፡

- ችሎቱ መካሄድ አለበት፤
- የችሎት ውሳኔ መሰጠት አለበት፤ እና
- የውሳኔው ግልባጭም ለእርስዎ፣ ለት/ቤት ዲስትሪክቱ እና Ohio Department of Education በተረጋገጠ መልእክት መላክ አለበት።

የመደበኛ ዳኝነት ስነ-ስርዓት ችሎት ከመጀመሩ ቢያንስ አምስት ቀናት በፊት እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ ይፋ በማድረጊያ ኮንፈረንስ ላይ መሳተፍ አለባችሁ። ይህ ውይይት የሚደረገው እርስዎና ዲስትሪክቱ በችሎት የሚቀርበው መረጃ ያላችሁ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።



### የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎቶች በገለልተኛ የችሎት መኮንን ሲካሄዱ

**የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ሊፈታ ካልቻለ፣ በገለልተኛ የችሎት መኮንን ወደሚመራ መደበኛ ችሎት ይተላለፋል፡፡ የችሎት መኮንኑ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎቶችን ለመምራት ከ Ohio Department of Education ሥልጠና የተሰጠው የሕግ ባለሙያ መሆን አለበት፡፡**

**የችሎት መኮንኑን ወጪ የሚሸፍነው የት/ቤት ዲስትሪክቱ ቢሆንም፣ ግለሰቡ ግን ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ነው። እሱ ወይም እሷ በት/ቤት ዲስትሪክት ወይም በሌላ የመንግስት ኤጀንሲ ተቀጣሪ ካለመሆናቸው ሌላ አንዱን ወገን ጠቅሞ ሌላኛውን የሚጎዳ ግላዊ ወይም ሙያዊ ጥቅም ሊኖረው አይገባም።**

**በተጨማሪም፣ የችሎት መኮንኑ የፌዴራል የግዛት ሕግጋትና ደንቦችን ጨምሮ የልዩ ትምህርት መስፈርቶችንና ፍ/ቤቶችም የልዩ ትምህርት ጉዳዮችን እንዴት መተርጎም እንዳለባቸው ጭምር በቂ ግንዛቤ አለው።**

**ከችሎቱ በኋላ፣ ችሎት መኮንኑ በመደበኛው የሕግ አሰራር መሰረት ውሳኔ ይጽፋል። ዲስትሪክቱ ወይም የችሎት መኮንኖችን ዝርዝር ከትምህርት ደረጃቸው ጋር መስጠት ይችላል፣ ወይም እርስዎ education.ohio.govየሚለው ድረ ገጽ በመጎብኘት ቀጣዩን ቁልፍ የመፈለጊያ ቃል በማስገባት *due process hearing officers*ያገኛሉ።**

### የችሎት መብቶች

በመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ላይ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፦

- ችሎቱ የሚመለከተው ልጅ በችሎቱ ላይ እንዲገኝ የማድረግ፤
- ችሎቱ ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆን የመጠየቅ፤
- ጠበቃዎ ወይም አካል ጉዳተኛ ልጆችን በተመለከተ ልዩ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ከእርስዎ ጋር ሆነው እንዲያማክሩዎት የማድረግ፤
- ማስረጃ የማቅረብ፣ ለምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብና ምስክሮች እንዲገኙ የመጠየቅ (በድጋሚ፣ ዲስትሪክቱ አዳዲስ ጉዳዮችን እንዲያነሱ ካልፈቀደልዎ በስተቀር ችሎቱ የሚሸፍነው ጉዳይ እርስዎ በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ቅሬታዎ ላይ ያነሷቸውን ነጥቦች ብቻ ነው)፤
- ከችሎት ቢያንስ አምስት ቀናት በፊት ለእርስዎ ያልደረሰው ማንኛውም ማስረጃ እንዳይቀርብ የመቃወም፤ እና
- የችሎቱን ሒደት እና ማንኛውም ግኝትና ውሳኔ የጽሑፍ ግልባጭ ወይም የኤሌክትሮኒክ ኮፒ ከክፍያ ነጻ የማግኘት መብት አለዎት።

#### ጠበቃ ያልሆነ የሕግ ባለሙያ አብሮዎት ካለ

ጠበቃ ያልሆነ የሕግ ባለሙያ አብሮዎት ካለ፣ ግለሰቡ ከሌላኛው ወገን የጠበቃ ክፍያ (ወይም የአገልግሎት ክፍያ) የመቀበል መብት የለውም። የሕግ ባለሙያው በችሎት ቆሞ መከራከር የማይችል ሲሆን በዳኝነት ሒደቱ ወቅትም ተሳትፎው ሊገደብ ይችላል።

### የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታዎችና የጊዜ ሰሌዳ

የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ማለት የተወሰኑ የልዩ ትምህርት አለመግባባቶችን በተፋጠነ ሁኔታ መፍታትን የሚያመቻች የተፋጠነ ችሎት ነው። እርስዎ ወይም ዲስትሪክቱ የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት መጠየቅ የምትችሉት በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፦

1. የት/ቤት ዲስትሪክቱ የልጅዎን ትምህርታዊ ምደባ (ፕሮግራም ወይም አገልግሎቶች) በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ፣ እና የዚህም ምክንያት ት/ቤቱ በልጅዎ ላይ የዲስፕሊን እርምጃ በመውሰዱ ከሆነ፤ ወይም
2. በማኒፌስቴሽን ውሳኔ ውጤቶች ካልተስማሙ፤ ወይም
3. በት/ቤት ዲስትሪክቱ እምነት የልጅዎ ወቅታዊ የትምህርት ምደባ (ፕሮግራም ወይም አገልግሎቶች) በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት የማድረስ ዕድሉ ከፍተኛ ከሆነ።

የተፋጠነ መደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ የጊዜ ሰሌዳ የ15 ቀናት የመፍትሔ ጊዜን እና የ20 የትምህርት ቀናት የችሎት ጊዜ ሰሌዳን ያካትታል። የት/ቤት ዲስትሪክቱ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ በደረሰው በሰባት የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሔ ስብሰባን ጊዜ መወሰን አለበት። የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የችሎት መኮንኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ለመጻፍና ለእርስዎና ለዲስትሪክቱ ለመላክ 10 የትምህርት ቀናት አሉት። የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ ሲቀርብ ተጨማሪ ጊዜ አይሰጥም።



## በውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ

ቅሬታ ያደረበት ወገን ውሳኔውን በተቀበለ በ45 ቀናት ውስጥ ይግባኙን በቀጥታ ለOhio Department of Education ካላቀረበ በስተቀር የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ሲጠናቀቅ በገለልተኛ የችሎት መኮንን የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ቅሬታ የገባው ወገን የችሎት መኮንኑ ውሳኔ ያልተስማማው (በውሳኔው የተሸነፈው ወገን) ወላጅ ወይም ዲስትሪክት ሊሆን ይችላል።

### የችሎት መኮንኑን ውሳኔ እንዴት ይግባኝ ማለት እንደሚቻል

የችሎት መኮንኑ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለመጠየቅ፣ የይግባኝዎን ኮፒ በጽሑፍ አድርገው ለዲፓርትመንቱ እና የይግባኙን ኮፒ ለት/ቤት ዲስትሪክትዎ ዋና ተቆጣጣሪ መላክ አለብዎ። ዲፓርትመንቱ መደበኛ የዳኝነት ውሳኔን ገለልተኛ ግምገማ የሚያካሂድ ግዛት አቀፍ የግምገማ መኮንን ይሰይማል። የOhio Department of Education የግምገማ መኮንኑን ወጪ ይሸፍናል። የግምገማ መኮንኑ አጠቃላይ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት መዛግብትን ይመረምራል። በተጨማሪ፣ የግምገማ መኮንኑ ችሎቱ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ሒደት መስፈርቶችን መከተሉን በማረጋገጥ አስፈላጊነቱ የታመነበትን ተጨማሪ ማስረጃ ያፈላልጋል። የግምገማ መኮንኑ ከእርስዎና ከት/ቤት ዲስትሪክቱ የቃል ወይም የጽሑፍ ክርክሮች እንዲካሄዱ ሊጠይቅ ይችላል። የግምገማ መኮንኑ የቃል ክርክሮችን ለመስማት ችሎት ካካሄደ፣ በመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ለእርስዎ የተሰጡ የችሎት መብቶች (ገጽ 25 ተመልከት) በሙሉ በችሎቱ ወቅትም ለእርስዎ ይፈቀዳሉ።

#### የገለልተኛ የችሎት መኮንን ውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ

የገለልተኛ የችሎት መኮንን ውሳኔ በደረሰዎት በ45 የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን መቃወም (ይግባኝ መጠየቅ) ይችላሉ። ይግባኝዎን በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡

Ohio Department of Education
Office for Exceptional Children
Dispute Resolution Section
25 South Front Street
Mail Stop 409
Columbus, Ohio 43215

ለተጨማሪ እገዛ፣ እባክዎ ለOhio Department of Education
Office for Exceptional Children
Attn: በስልክ ቁጥር፡ (614) 466-2650 ወይም ከክፍያ ነጻ (877) 644-6338 ይደውሉ።

### የጊዜ ሰሌዳ/ማራዘሚያዎች

ዲፓርትመንቱ ግዛት አቀፍ ግምገማ እንዲካሄድልዎ ጥያቄዎትን ባቀረቡ በ30 ቀናት ውስጥ የግምገማ መኮንኑ የጊዜ ማራዘሚያ ካልሰጠ በስተቀር ውሳኔ መስጠት የሚችል ሲሆን የጊዜ ማራዘሚያን ወላጅ ወይም ዲስትሪክቱ ሊጠይቅ ይችላል (ይሁን እንጂ፣ የተፋጠነ መደበኛ የዳኝነት ስርዓት ችሎት ውሳኔ ይግባኝ ሲጠየቅ የጊዜ ማራዘሚያ ሊሰጥ እንደማይችል ያስተውሉ)። የግምገማ መኮንኑን ግኝትና ውሳኔ የጽሑፍ ግልባጭ ወይም የኤሌክትሮኒክ ኮፒ መጠየቅ ይችላሉ።

### ለፌዴራል ወይም ለግዛት ፍ/ቤት ይግባኝ መጠየቅ

ለፌዴራል ወይም ለግዛት ፍ/ቤት ይግባኝ ካልተጠየቀበት በስተቀር፣ የግዛት አቀፍ ግምገማ ውሳኔ የመጨረሻ ነው። በግምገማ መኮንኑ ውሳኔ ቅሬታ ያደረበት ወገን (ተሸናፊው ወገን) የግምገማ መኮንኑ ውሳኔ በደረሰው በ90 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ዲስትሪክት ፍ/ቤት ወይም የግምገማ መኮንኑ ውሳኔ በደረሰው በ45 ቀናት ውስጥ የልጅዎ ት/ቤት ዲስትሪክት ለሚገኝበት ካውንቲ የተለመዱ አቤቱታዎች ሰሚ ፍ/ቤት ክስ መመስረት ይችላል። ፍ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ወገኖች በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ማስረጃዎችን ይገመግማል፣ ተጨማሪ ማስረጃዎችንም አዳምጦ በቀረቡለት መዛግብትና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል። ለፍ/ቤት ላቀረቡት ይግባኝ ወጪዎን የሚሸፍኑት እርስዎ ሲሆኑ፣ ይግባኝዎት ተቀባይነት ካገኘም በፍ/ቤቱ ፈቃደ ስልጣን መሰረት የዳኝነት ክፍያና የጠበቃ ወጪዎት (ገጽ 28 ተመልከት)ይሸፈንልዎታል።

## በመደበኛ የዳኝነት ስነ-ስርዓት ሒደት ወቅት የልጁ ሁኔታ

- እርስዎና የት/ቤት ዲስትሪክቱ የልጅዎ ትምህርታዊ ምደባ ሊቀየር እንደሚችል ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ቅሬታ በሒደት ላይ እያለ ልጅዎ አሁን ባለበት የትምህርት ምደባ ውስጥ መቆየት አለበት።
- የልጅዎ ወቅታዊ ትምህርታዊ ምደባ በቅርብ ጊዜ በተተገበረው IEP ውስጥ የተገለጸው ነው።
- ልጅዎ በት/ቤት ዲስትሪክቱ የዲስፕሊን እርምጃ ምክንያት በጊዜያዊ የትምህርት ማዕቀፍ ((IAES – ከት/ቤት ውጭ ያለ ጊዜያዊ የመማሪያ አደረጃጀት) ውስጥ ከተመደበ፣ የችሎት መኮንኑ ውሳኔ እስከሚያሳልፍ ወይም ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ የወሰደው ዲስፕሊን እስከሚያበቃ ድረስ ልጅዎ በዚያ የትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ይቆያል፤
- የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ይግባኙ ወደ ዲስትሪክቱ መግባትን የሚያካትት ከሆነ፣ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት እስከሚጠናቀቅ ድረስ እርስዎ ከፈቀዱ ልጅዎ በዲስትሪክቱ ውስጥ መመደብ አለበት።
- የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ይግባኙ የሕጉን ለትምህርት የደረሰ ዕድሜ መሰረት በማድረግ አገልግሎቶችን የመጀመር ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነና የዚህ ምክንያቱም የልጅዎ ዕድሜ 3 ዓመት በመሙላቱና በቅድመ እርምጃ መሰረት ለሚሰጡ አገልግሎቶች ብቁ ባለመሆኑ ምክንያት ከሆነ፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ ልጅዎ ሳያገኛቸው የነበሩትን የቅድሚያ እርምጃ አገልግሎቶች ማቅረብ አይጠበቅበትም።
- ልጅዎ ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ከተገኘና ወላጅም አገልግሎቶቹ በመጀመሪያ እንዲሰጡ ከተስማማ፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ በወላጅና በዲስትሪክት መካከል አለመግባባት ያልተፈጠረባቸውን አገልግሎቶች ማቅረብ አለበት።
- የግምገማ መኮንኑ የምደባ ለውጥ አግባብነት ያለው ስለመሆኑ ከልጅዎ ወላጆች ጋር ከተስማማበት፣ ምደባው በግዛትና በወላጆች መካከል የተደረገ ስምምነት ተደርጎ ይቆጠራል።

## የጠበቃ ወጪ

በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ሒደት (ወይም የመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሲጠየቅበት) እርስዎን የሚወክል ጠበቃ መቅጠር የሚችሉ ቢሆንም የራስዎን የጠበቃ ወጪ መሸፈን አለብዎት። ጠበቃ ለመቅጠር ከፈለጉና በማንኛውም ክስ ወይም ከመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ጋር በተያያዘ የፍርድ ሒደት አሸናፊ ከሆኑ (አዎንታዊ ውሳኔ ካገኙ)፣ ፍ/ቤቱ ዲስትሪክቱ ምክንያታዊ የሆነ ጠበቃ ወጪ እንዲሸፍን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

### ዲስትሪክቱ ክሱን ካሸነፈ

ዲስትሪክቱ ክሱን ካሸነፈ ፍ/ቤቱ የዲስትሪክቱን ጠበቃ ምክንያታዊ ወጪ እንዲከፍሉ እርስዎን ሊያዝዎት ይችላል። የ Ohio Department of Education እና የት/ቤትዎ ዲስትሪክት ክሱን ካሸነፉና ፍ/ቤቱም የሚከተሉትን ውሳኔዎች ሲሰጥ እርስዎ ወይም ጠበቃዎ የእነርሱን የጠበቃ ወጪ እንዲሸፍኑ ትእዛዝ ሊሰጥዎ ይችላል፡

- ክሱ የተጭበረበረ፣ ኢ-ምክንያታዊ ወይም መሰረተ ቢስ እንደሆነ፤
- ክሱ የተጭበረበረ፣ ኢ-ምክንያታዊ ወይም መሰረተ ቢስ መሆኑ ከታወቀ በኋላ እርስዎ ክስ ማቅረብዎን ከቀጠሉ፤ ወይም
- ክሱ የቀረበው አግባብነት ለሌለው ዓላማ፣ ማለትም ለማስፈራራት፣ አላስፈላጊ መዘግየትን ለመፍጠር፣ ወይም የሕግ ነክ ወጪዎችን ያለአግባብ ለመጨመር ከሆነ።

### ፍ/ቤቱ የሕግ ወጪዎች ለእርስዎ ወይም ለዲስትሪክቱ ተመላሽ እንዲደረግ ያዛል

ፍ/ቤቱ የሕግ ወጪዎች ለእርስዎ ወይም ለዲስትሪክቱ ተመላሽ እንዲደረግ ካዘዘ፣ ፍ/ቤቱ ምክንያታዊ የሆነውን መጠን ይወስናል። የጠበቃ ወጪዎች ክሱ በቀረበበት አካባቢ ውስጥ በተለመደ የክፍያ ተመን ላይ እና በተሰጡት አገልግሎቶች ዓይነትና ጥራት ላይ የተመሰረተ ይሆናል። ፍ/ቤቱ የጠበቃ ወጪ እንዲከፈል የማዘዝ ሥልጣን የተወሰነ ገደብ አለው። ፍ/ቤት በሚከተሉት ሁኔታዎች የጠበቃ ወጪ እንዲከፈል ማዘዝ አይችልም፡

- ዲስትሪክቱ ክሱ በተመሰረተ በ10 ቀናት ውስጥ አለመግባባቱን ለመፍታት ጥሪ ካቀረበና እርስዎም የቀረበውን ጥሪ በ10 ቀናት ውስጥ ካልተቀበሉና በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ዲስትሪክቱ ጥሪውን ካቀረበበት መፍትሔ የባሰ ከሆነ፤
  - ይሁን እንጂ፣ በክሱ አሸናፊ ከሆኑና ዲስትሪክቱ ያቀረበልዎትን የግጭት መፍትሔ ላለመቀበል በቂ ምክንያት አለው ብሎ ፍ/ቤት ከወሰነ የጠበቃ ወጪዎ እንዲሸፈንልዎ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤
- ስብሰባው የተጠራው በ አስተዳደራዊ ችሎት ወይም በክስ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ጠበቃዎ በIEP ስብሰባ ላይ ለሚኖረው ተሳትፎ፤ እና
- ጠበቃዎ በመፍትሔ ስብሰባ ላይ ለሚኖረው ተሳትፎ ነው።

### የጠበቃ ወጪን መቀነስ

ፍ/ቤቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች የጠበቃ ወጪ እንዲከፈል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡

- ክሱ በሒደት ላይ እያለ እርስዎ ወይም ጠበቃዎ ያለመግባባቱን የመጨረሻ መፍትሔ ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ ካዘገያችሁ፤
- የጠበቃዎ ወጪ ተመሳሳይ ክህሎት፣ ዝና እና ልምድ ያላቸው ተመሳሳይ የሚሰጡ ሌሎች ጠበቆች ከሚያስከፍሉት ክፍያ ጋር ሲነጻጸር በተጋነነ ሁኔታ የበለጠ ከሆነ፤
- ከክሱ ወይም ከፍርድ ሒደቱ አንጻር ለአገልግሎት የጠፋው ጊዜ እና ያገኙት የሕግ አገልግሎት በጣም የበዛ ከሆነ፤ጠበቃዎ በእርስዎ የቅሬታ ማቅረቢያ ላይ ለት/ቤቱ አግባብነት ያለው መረጃ ካላቀረበ።

ግዛቱ ወይም የት/ቤት ዲስትሪክቱ የክሱን ወይም የፍርድ ሂደቱን መፍትሔ ያለአግባብ እንዳዘገዩ ወይም የ IDEA የአሰራር ዋስትናዎችን መጣሳቸው በፍ/ቤት ከተረጋገጠ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተፈጻሚ አይሆኑም።

# ዲስፕሊን

## አካል ጉዳተኛ ሕጻናት ላይ የሚተገበሩ የዲስፕሊን አሰራሮች

ዲስትሪክቱ ልጅዎን አሁን ካለበት የትምህርት ምደባ ካገደ፣ ካባረረ ወይም በሌላ መልኩ ካስወጣ በኋላም (አሁን ያለበትን የትምህርት ምደባ በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ የልጅዎን IEP ይመልከቱ) ቢሆን በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የት/ቤት ዲስትሪክትዎ ለአካል ጉዳተኛ ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች መስጠቱን ሊቀጥል ይችላል።

### የትምህርት ምደባ እና አማራጮች

ልጅዎ ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ለሚያንስ ጊዜ የት/ቤት ዲስትሪክት ደንቦችን በመጣሱ ምክንያት አሁን ካለበት የትምህርት ምደባ ከተባረረ፣ ዲስትሪክቱ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መስጠት አይጠበቅበተም። ልጅዎ *ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት* ለሚበልጥ ጊዜ ከት/ቤት ከተባረረ፣ ልጅዎ በሌላ የትምህርት ማዕቀፍ (ለምሳሌ በሌላ የመማሪያ ክፍል፣ ሕንጻ ወይም በተማሪው ቤት) ቢሆንም እንኳን ት/ቤቱ ለልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች መስጠቱን ሊቀጥል ይገባል።

የት/ቤት ዲስትሪክቱ ልጅዎ አሁን ካለበት ምደባ በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ ካባረረው፣ የልጅዎ የትምህርት ምደባ እንደተቀየረ ይቆጠራል።

የት/ቤት ዲስትሪክቱ ልጅዎ አሁን ካለበት ምደባ በተለያዩ ጊዜያት (በተደጋጋሚ ማባረር)ካባረረና የተባረረባቸው ቀናትም ድምር በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ከ10 ቀናት ከበለጠ፣ እነዚህ የማባረር ቅጣቶቹ የልጅዎ የትምህርት ምደባ መቀየሩን የሚያመላክት ስለመሆኑ ዲስትሪክቱ መወሰን አለበት። ዲስትሪክቱ ይህን ውሳኔ ሲወስን የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡

- ልጅዎ ተባርሮ የቆየበት ጊዜ እርዝመት፤
- ልጅዎ የተባረረባቸው ጊዜያት ብዛት፤
- የተባረረባቸው ጊዜያት መቀራረብ፤ እና
- ልጅዎ ከተባረረባቸው የበፊት ክስተቶች ላይ ያሳየው የባሕርይ ተመሳሳይነት።

ልጅዎ የት/ቤት ሕጎችን ባለማክበሩ የተነሳ የትምህርት ምደባው ሲቀየር፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ፣ ወላጅ ወይም አግባብነት ያለው የIEP ቡድን አባል የማኒፌስቴሽን አወሳሰን ግምገማ ለማካሄድ ስብሰባ ማድረግ አለባቸው። የማኒፌስቴሽን አወሳሰን ግምገማ ዓላማ የልጅዎ ባህርይ መንስኤ ከአካል ጉዳት ጋር ቀጥተኛ ወይም የጎላ ትስስር ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።



## የማኒፌስቴሽን አወሳሰን

የት/ቤት ዲስትሪክቱ በዲስፕሊን ጉዳይ የተነሳ የልጅዎን የትምህርት ምደባ ከመቀየሩ በፊት የልጅዎን መብቶች ለመጠበቅ የተወሰኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። አንደኛው እርምጃ የማኒፌስቴሽን አወሳሰን ግምገማ ስብሰባ ነው። የዚህ ስብሰባ ዓላማ የልጅዎ ባህርይ በአካል ጉዳቱ ምክንያት የተከሰተ ወይም ቀጥተኛና የጎላ ትስስር ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። በሌላ አነጋገር፣ የልጅዎ ባህርይ መንስኤ አካል ጉዳቱ ነው? የተማሪው IEP ቡድን የትምህርት ምደባን ለመቀየር ውሳኔ በተላለፈ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ የልጅዎ ባህርይ በአካል ጉዳቱ ምክንያት የተከሰተ መሆን አለመሆኑን ይወስናል።

**እባክዎ ያስተውሉ**

**ልጅዎ በት/ቤቱ የሚማሩ ማናቸውም ተማሪዎች ላይ የሚተገበሩ ደንቦችና ዲስፕሊን ተፈጻሚ የሚደረግበት ሲሆን በተመሳሳይ ምደባ ውስጥ ባይሆንም እንኳን በIEP ውስጥ የተገለጹ አገልግሎቶችን ማግኘቱን ይቀጥላል።**

### የማኒፌስቴሽን አወሳሰን ግምገማ ስብሰባ

በማኒፌስቴሽን አወሳሰን ግምገማ ስብሰባ ወቅት እርስዎና ሌሎች የIEP ቡድን አባላት የልጅዎን IEP፣ የመምህር ምልከታዎችና ማናቸውም የቀረቡ ተዛማጅ መረጃዎችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ይገመግማሉ።

ባህርይው የልጅዎ አካል ጉዳት ነጸብራቅ ከሆነ፣ የ IEP ቡድን ምደባውን ለመቀየር ካልተስማማ በስተቀር ልጅዎ ወደተባረረበት ምደባ ይመለሳል።

የልጅዎ ባህርይ የአካል ጉዳት ነጸብራቅ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የ IEP ቡድኑ፡

1. በ10 ቀናት ውስጥ ተግባራዊ የባህርይ ምዘና መጀመርና በተቻለ ፍጥነት ማጠናቀቅ አለበት። ተግባራዊ የባህርይ ምዘና የልጅዎ ባህርይ ምዘና ሲሆን በልጅዎ ከባቢ ውስጥ አግባብነት የጎደለው ባህርይን የሚያነሳሱ ነገሮች ምን እንደሆና ማስተማር የሚገባ የምደባ ባህርያት የትኞቹ እንደሆኑ በመወሰን ልጅዎ አዎንታዊ ውጤቶችና ግብረ መልስ እንዲያገኝ የሚያስችል ነው፤
2. ተግባራዊ የባህርይ ምዘና ቀደም ሲል ከተካሄደና አሁን ካለው ዲስፕሊን ጋር ተያያዥነት ካለው ለልጅዎ የባህርይ ጣልቃ ገብነት ዕቅድን መጀመር፡ ፡ (የባህርይ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ በት/ቤት ውስጥ አግባብነት የሌላቸውን ባህርያትና ት/ቤቱም እነርሱን ለመቀነስ የሚሞክርባቸው መንገዶችን የሚመለከት ነው።)፤ ወይም
3. የባህርይ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ ቀደም ሲል ያለ ከሆነ፣ ዕቅዱን ከልሰው በ10 ቀናት ውስጥ ማናቸውንም አስፈላጊ ማሻሻያዎች ማድረግ።



## ጊዜያዊ የአማራጭ (ጊዜያዊ እና የተለየ) ትምህርት ማዕቀፍ

በጊዜያዊ የትምህርት ማዕቀፍ (IAES) ልጅዎን ለመመደብ ውሳኔ የሚያሳልፈው የልጅዎ IEP ቡድን ነው። IAES ልጅዎ ልዩ ትምህርት የሚያገኙበት ጊዜያዊና የተለየ ምደባ ነው። ልጅዎ የት/ቤት ሕጎችን ባለማክበሩ የተነሳ የIEP ቡድኑ የልጅዎን ምደባ ወደ IAES ለመቀየር በሚወስንበት ቀን የት/ቤት ዲስትሪክቱ ውሳኔውን ሊያሳውቅዎትና ይህን ወላጆች በልዩ ትምህርት ውስጥ ያላቸውን መብት የሚመለከት መምሪያ ሊሰጥዎት ይገባል።

የልጅዎ ባህርይ በአካል ጉዳት ምክንያት የተከሰተ ቢሆንም እንኳን ልጅዎ የሚከተሉትን ድርጊቶች ከፈጸመ ዲስትሪክቱ ልጅዎን እስከ 45 የትምህርት ቀናት ወደ IAES ሊያዛውረው ይችላል፡

- የጦር መሳሪያ ይዞ ከተገኘ፤
- ሆነ ብሎ ሕገ-ወጥ ዕፆችን ይዞ ከተገኘ ወይም ከተጠቀመ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትን ንጥረ ነገር (ለምሳሌ ናርኮቲክስ) ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ከሞከረ፤ ወይም
- በሌላ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ካደረሰ።

ባጠቃላይ ይህ ተፈጻሚነት የሚኖረው ልጅዎ ድርጊቱን የፈጸመው ወደ ት/ቤት እየሄደ፣ በት/ቤት እያለ ወይም የት/ቤት ተግባር ላይ እያለ ከሆነ ነው።

የልጅዎ ባህርይ ***ከአካል ጉዳቱ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ከሌለው፣*** ልጅዎ አካል ጉዳት የሌለበት ልጅ ላይ ከሚወሰን የቅጣት ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ለሆነ ጊዜ በ IAES ውስጥ ሊመደብ ይችላል።

የልጅዎ ባህርይ ***ከአካል ጉዳቱ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ከነበረውና*** ልጅዎም የት/ቤት ሕጎችን ከጣሰ፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ በባህርያዊ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ ወይም IEP ውስጥ በሚደረግ ለውጥ ምክንያት ምደባውን ለመቀየር ካልተስማማ በስተቀር ልጅዎ ወደተባረረበት የትምህርት ማዕቀፍ መመለስ አለበት።

ይሁን እንጂ፣ ዲስትሪክቱ ልጅዎን አሁን ባለበት የትምህርት ምደባ (በልጅዎ መሰረት) ማቆየቱ በልጅዎ ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት የማስከተል ዕድሉ ከፍተኛ ነው ብሎ ካመነ፣ የት/ቤት ዲስትሪክቱ በጉዳዩ ላይ ለመወያየት የ IEP ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። እርስዎና ዲስትሪክቱ በምደባ ለውጡ ላይ ካልተስማማችሁ፣ ዲስትሪክቱ የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ችሎት ሊጠይቅ ይችላል፤ በሌላ አነጋገር፣ ፈጣን መፍትሔ የሚሰጥ የመደበኛ ዳኝነት ችሎት እንዲዘጋጅ ይጠይቃል (የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነትን ገጽ 25 ላይ ተመልከት)።

### በትምህርት ምደባ ለውጥ ወይም በማኒፌስቴሽን አወሳሰን ግምገማ ችሎት ግኝት ካልተስማሙ

በዲስፕሊን ምክንያት የልጅዎ ወቅታዊ የትምህርት ማዕቀፍ እንዲቀየር የተወሰነውን ውሳኔ ወይም የማኒፌስቴሽን ግምገማ ችሎት ግኝትን ለመቃወም የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። (የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ሒደትን ገጽ 24-25 ተመልከት)። ገለልተኛው የችሎት መኮንን የት/ቤት ዲስትሪክቱ የልጅዎን ምደባ በቀየረበት ወቅት የተቀመጡ መስፈርቶችን መከተሉን ወይም የልጅዎ ባህርይ የአካል ጉዳቱ ነጸብራቅ እንደነበር ወይም እንዳልነበር አሳይቷል የሚለውን ጉዳይ በተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ወቅት ይወስናል። ከላይ እንደተጠቀሰው፣

ዲስትሪክቱ የልጅዎን ምደባ መቀጠሉ በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት የማስከተል ከፍተኛ ዕድል እንዳለው ካመነበት የት/ቤት ዲስትሪክቱ የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነት ስርዓት ችሎት ሊጠይቅ ይችላል። (የተፋጠነ የመደበኛ ዳኝነትን ገጽ 25 ላይ ተመልከት)።

**የልጅዎ ባህርይ በተጠርጣሪ የአካል ጉዳት ምክንያት ሲሆን**

**ልጅዎ IEP ከሌለው፣ ት/ቤቱ ልጅዎን እንደ አካል ጉዳተኛ ልጅ እንዲቆጥረው መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን ለዚህም ሁኔታ ልጅዎ የት/ቤቱን ሕግ ከመጣሱ በፊት የሚከተሉት ነገሮች መከሰት አለባቸው፡**

- **ለልጅዎ መምህር የት/ቤት መሪዎች ልጇ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ያስፈልገዋል ብለው እንደሚያስቡ ከነገሯቸው፤ ወይም**
- **ልጅዎ ላይ ምዘና እንዲካሄድ ከጠየቁ፤ ወይም**
- **የልጅዎ መምህር ወይም ሌላ የት/ቤት ዲስትሪክት ሠራተኛ የልጅዎን ባህርያዊ ሁኔታ በተመለከተ የተወሰኑ አሳሳቢ ጉዳዮችን ለልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ወይም ሌሎች የስራ አመራር አባላት በቀጥታ ካሳወቀ።**

**ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ የልዩ ትምህርት ምዘና እንዲያካሂድ ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ የት/ቤትዎ ዲስትሪክት ልጅዎን እንደ አካል ጉዳተኛ ሕጻን መቁጠር አይጠበቅበትም፡ ፡ ለልጅዎ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዳይሰጡት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ለልጅዎ ምዘና ተደርጎለት ልጅዎ የአካል ጉዳት እንደሌለበት ቡድኑ ከወሰነም ይኸው ተፈጻሚ ይሆናል። ዲስትሪክቱ በልጅዎ ላይ የሚወስደው ዲስፐሊን እርምጃ ተመሳሳይ ባህርይ የሚያሳዩ ጉዳት አልባ ልጆች ላይ ከሚወስደው የዲስፐሊን እርምጃ ጋር ተመሳሳይ ነው።**



# ወላጆች አካል ጉዳተኛ ልጆችን በግል ት/ቤት በማስገባት ወጪው በመንግስት የሚሸፈንበት ሁኔታ

## የወጪ ምልሰት አወሳሰን ሒደት

ልጅዎን በግል ት/ቤት ለማስገባት ከፈለጉ፣ ዲስትሪክቱ ለልጅዎ አግባብነት ያለው የመንግስት ትምህርት በነጻ (FAPE) እስካቀረበ ድረስ ልጅዎ በግል ት/ቤት ውስጥ ለሚያገኘው ትምህርት ወይም ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ወጪን ዲስትሪክቱ የመሸፈን ግዴታ የለበትም። ዲስትሪክትዎ አግባብነት ያለው የመንግስት ትምህርት በነጻ ለልጅዎ ማቅረብ አልቻለም ብለው ካመኑ፣ መደበኛ የዳኝነት ስርዓት ቅሬታ የማቅረብ መብት ስላለዎት ችሎት ተዘጋጅቶ ገለልተኛ የችሎት መኮንንም ዲስትሪክቱ ለልጅዎ አግባብነት ያለው የመንግስት ትምህርት በነጻ ማቅረብ አለማቅረቡን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል (መደበኛ የዳኝነት ስርዓትን የሚመለከት መረጃን ገጽ 21-27 ላይ ተመልከት)። በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ሂደት ወቅት ዲስትሪክቱ ለልጅዎ አግባብነት ያለው የመንግስት ትምህርት በነጻ ማቅረብ አለማቅረቡ በገለልተኛ የችሎት መኮንን ከተወሰነ፣ የችሎት መኮንኑ ልጅዎን በግል ት/ቤት ለማስመዝገብና ለማስተማር ያወጡት ወጪ ተመላሽ እንዲደረግልዎ ሊወስን ይችላል።

### ተመላሽ ክፍያን መቀነስ ወይም ቀሪ ማድረግ

ዲስትሪክቱ ለእርስዎ ተመላሽ የሚያደርገው የክፍያ መጠን ሊቀንስ ወይም እርስዎ ተመላሽ ሂሳቡን ቀሪ ሊያደርጉት የሚችሉት በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡

- እርስዎ ልጅዎን ከት/ቤት ከማስወጣትዎ በፊት በተካሄደ የ IEP ስብሰባ ላይ የIEP ቡድኑ የጠቆመውን የትምህርት ምደባ እንደማይቀበሉትና ስለሚያሳስብዎ ጉዳይ ካልነገሯቸውና ልጅዎን በግል ት/ቤት ውስጥ ለማስመዝገብ ማቀድዎን ካላሳወቁ፤ ወይም
- ልጅዎን ከዲስትሪክቱ ከማስወጣትዎ ቢያንስ ከ10 የስራ ቀናት በፊት IEP እንደማይቀበሉትና ልጅዎን በግል ት/ቤት ውስት ለማስመዝገብ ማቀድዎን ለት/ቤቱ በጽሑፍ ካላሳወቁ። እነዚህ 10 የስራ ቀናት በስራ ቀናት ላይ የሚውሉ የበዓል ቀናትን ይጨምራሉ፤ ወይም
- ልጅዎን ከት/ቤት ከማስወጣትዎ በፊት ዲስትሪክቱ ልጅዎ ላይ ምዘና ለማካሄድ ማቀዱን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ከሰጠዎትና እርስዎም ልጅዎን ለምዘናው ዝግጁ ካላደረጉ፤ ወይም
- ፍ/ቤቱ የእርስዎ ድርጊት ምክንታዊ አይደለም ብሎ ከወሰነ ነው።

### የወጪ ምልሰት ጥበቃ

ተመላሽ የሚደረግልዎ ገንዘብ ሊቀነስ ወይም ሊከለከል የማይችልባቸው ሁኔታዎች፡

- ዲስትሪክቱ ማስታወቂያ ከመስጠት ከከለከለዎ፤
- ዲስትሪክቱ ማስታወቂያ መስጠት እንዳለብዎ ካልነገረዎ፤ ወይም
- ማስታወቂያውን መስጠት በልጅዎ ላይ የአካል ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ።

በተጨማሪም፣ ፍ/ቤት ወይም የችሎት መኮንን ማስታወቂያ ባለመስጠት ምክንያት ተመላሽ የሚደረግልዎ ወጪ ሊቀነስ ወይም ሊከለከል የማይችልባቸውን ሁኔታዎች ያስቀምጣል፡

- እንግሊዝኛ ቋንቋ ማንበብ ወይም መጻፍ የማይችሉ ከሆነ፤ ወይም
- ማስታወቂያውን መስጠት በልጅዎ ላይ ከባድ የስሜት ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ነው።



# የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ስኮላርሺፕ ፕሮግራሞችን ለወላጅ ማሳወቂያ

## ማሳወቂያ ሲላክ

የት/ቤት ዲስትሪክት አካል ጉዳተኛ ሕጻን ላይ ምዘና ሲያካሂድ ወይም የልጁን IEP ማዘጋጀት፣ መከለስ ወይም መገምገም ሲጀምር፣ ዲስትሪክቱ ለልጅዎ ወላጆች ስለ Autism Scholarship Program እና Jon Peterson Scholarship Program መንገር አለበት።

### Autism Scholarship Program

ልጅዎ በኦቲዝም ምድብ ስር የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘ ከሆነ፣ ለ Autism Scholarship Program ብቁ ሊሆን ይችላል። በዚህ ፕሮግራም መሰረት እርስዎ የሚኖሩበት ት/ቤት ዲስትሪክት ከሚሰጠው የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ውጭ ወዳለ ሌላ ፕሮግራም ልጅዎን መላክ የሚችሉ ሲሆን በዚያም ልጅዎ በ IEP ውስጥ የተዘረዘሩትን ትምህርትና አገልግሎቶች ያገኛል።

ልጅዎ ለፕሮግራሙ ብቁ ለመሆን፡

- ኦቲዝም ያለበት ሕጻን መሆኑ በአካባቢው የት/ቤት ዲስትሪክት መረጋገጥ አለበት፤
- እርስዎ የተስማሙበትና የተጠናቀቀ IEP ከሚኖሩበት የት/ቤት ዲስትሪክት የተላከ ሊኖር ይገባል፤ እና
- ዕድሜው ቢያንስ ሶስት ዓመት ሊሆን ይገባል።

ስለ Autism Scholarship Program መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን የ Ohio Department of Education ድረ ገጽ በመጎብኘት education.ohio.gov በመፈለጊያ ሳጥኑ ውስጥ ***Autism Scholarship Program***ብለው ይጻፉ ወይም በኢሜል ይጻፉ **autismscholarship@education.ohio.gov**።

### Jon Peterson Special Needs Scholarship Program

ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘ ከሆነ፣ ለ Jon Peterson Special Needs Scholarship Program ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ፕሮግራም መሰረት እርስዎ የሚኖሩበት ት/ቤት ዲስትሪክት ከሚሰጠው የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ውጭ ወዳለ ሌላ ፕሮግራም ልጅዎን መላክ የሚችሉ ሲሆን በዚያም ልጅዎ በ IEP ውስጥ የተዘረዘሩትን ትምህርትና አገልግሎቶች ያገኛል።

ልጅዎ ለ Jon Peterson Special Needs Scholarship Program ብቁ ለመሆን፡

- አካል ጉዳተኛ ሕጻን መሆኑ በአካባቢው የት/ቤት ዲስትሪክት መረጋገጥ አለበት፤
- እርስዎ የተስማሙበትና የተጠናቀቀ IEP ከሚኖሩበት የት/ቤት ዲስትሪክት የተላከ ሊኖር ይገባል፤ እና
- ከአፀደ ሕጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ለመማር ብቁ መሆን አለበት።

Jon Peterson Special Needs Scholarship Program በተመለከተ መረጃ ለማግኘት፣ የ Ohio Department of Education ድረ ገጽ የሆነውን education.ohio.gov በመጎብኘት በመፈለጊያ ሳጥን ውስጥ ***Jon Peterson Scholarship*** ብለው ይጻፉ ወይም በኢሜይል ይጻፉ፡ **peterson.education.ohio.gov**።

### ተጨማሪ መረጃ

የስኮላርሺፕ ፕሮግራሞችን የሚመለከት መረጃ ከቀጣዩ የ Ohio Department of Education ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፡ **education.ohio.gov**።

እነዚህን የስኮላርሺፕ ፕሮግራሞች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም ጥያቄ ለማቅረብ፣ ቀጣዩን አካል ያነጋገሩ፡ The Office of Nonpublic Educational Options ስልክ ቁጥር (614) 466-5743 ወይም ከክፍያ ነጻ ስልክ፡ (877) 644-6338።

Ohio | Department of Education

education.ohio.gov